# Freedom of Expression and Hate Speech in Ethiopia: Observations

Aron Degol ♣ & Bebizuh Mulugeta♣♣

## Abstract

Freedom of expression is one of the human rights enshrined under International human right instruments. However, hate speech in the course of exercising this right has the potential to pose threats on the peace and security of nations and wellbeing of individuals. This has brought about arguments in favor of limitations to expression and against the limitations owing to unintended adverse impact of such limitations in the exercise of freedom of expression. In the Ethiopian case, '*Hate Speech and Disinformation Prevention and Suppression Proclamation No. 1185/ 2020*' has been enacted. The Proclamation indicates prohibited acts of *hate speech* and its exceptions. In particular, the generic terms contained in the definition given to 'hate speech' need to be carefully examined. However, the implications of provisions that set exceptions to 'hate speech' in the new law have not yet been subject to adequate academic discourse. This article examines these issues. By consulting different international human rights instruments, experience of other countries and scholarly literature, the article examines the appropriateness, constitutionality and implications of the Proclamation on the right to freedom of expression. Moreover, it indicates potential challenges that the exceptions will pose on the process of implementing the Proclamation in real court cases.

## Key terms:

Freedom of expression · Hate speech · FDRE Constitution · Ethiopia

**DOI** http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v15i1.7

This article is licensed under a Creative Commons Attribution-NonCommercial-NoDerivs (CC BY-NC-ND)

**Received**: 31 March 2021 **Accepted**: 3 July 2021

**Suggested citation**:

Aron Degol & Bebizuh Mulugeta (2021), 'Freedom of Expression and Hate Speech in Ethiopia: Observations' (in Amharic), 15 *Mizan Law Review* 1: 195-226

♣ Aron Degol Habtu (LLB, LLM, MBA), Lecturer of Law and Management at St. Mary University
ORCID: https://orcid.org/0000-0002-6035-2222

♣♣ Bebizuh Mulugeta Menkir (LLB, LLM), Lecturer of Law, University of Gondar, School of Law, Former Public Prosecutor at Federal Attorney General's Office
ORCID:https://orcid.org/0000-0002-5026-2282

# ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትና የጥላቻ ንግግር ሕግ በኢትዮጵያ፣ አጭር ምልከታ

አሮን ደጎል* እና በብዙህ ሙሉጌታ**

**አህጽሮተ ይዘት** (Abstract)

ሰው በመሆን ብቻ ከሚገኙ የተለያዩ ሰብዓዊ መብቶች መካከል አንዱ ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ነው። ሆኖም ግን ሓሳብን በነፃነት በመግለጽ ሂደት የሚደረጉ የጥላቻ ንግግሮች በአገራት ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም በሰው ልጆች ደህንነት ላይ በሚያስከትሉት ከፍተኛ አደጋ ምክንያት፣ ይህንን ድርጊት ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ ገደቦች ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የሚያስረዱ ወገኖች አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ስለጥላቻ ንግግር የሕግ ትርጓሜ ለመስጠት በሚደረግ ጥረት ውስጥ በሕግ ጥበቃ እና እውቅና ባገኘው ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ አላስፈላጊ ጫና የሚፈጥር መሆኑን በማንሳት፣ ሓሳብን በመግለጽ ነፃነት ላይ ገደብ የሚያደርጉ ሕጎችን መውጣት የሚቃወሙ አስተያየቶች አሉ። በኢትዮጵያም የጥላቻ ንግግርን የመቆጣጠር ሕግ በማስፈለጉ የጥላቻ ንግግርን እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አዋጅ ቁጥር 1185/2012 ወጥቷል። ይህ አዋጅ እንደ ጥላቻ ንግግር የሚወሰዱ ተግባራትንና ልዩ ሁኔታዎችን አካቶ እናገኛለን። እንደሌሎች አገሮች ሁሉ ይህ አዋጅ ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ የሚያስከትለው የጎንዮሽ ጉዳት ሊነሳ ይችላል። ለምሳሌ የጥላቻ ንግግር ጥቅል ሆኖ መተርጎሙ እና የንግግር ነፃነትን የሚገድብ መሆኑ አጠያያቂ ያደርገዋል። በሌላ በኩል በዚህ አዋጅ እንደ ጥላቻ ንግግር እንዳይወሰዱ በልዩ ሁኔታነት የተቀመጡ ንግግሮች/ድርጊቶች የሕጉን አፈፃፀም እና የታለመለትን ዓላማ ያሳካ ዘንድ የሚኖራቸውን እንድምታ በሚመለከት የሓሳብ ልውውጥ አስፈላጊ ነው። ይህ ጽሑፍ እነዚህን ርዕሠ ጉዳዮች በማንሳት ዓለምአቀፍ እና አገርአቀፍ የሰብዓዊ መብትን የተመለከቱ የሕግ ማዕቀፎችን፣ የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ በተለያዩ ጸሐፍት የተዘጋጁ ጽሑፎችን በማጣቀስ፣ ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ከጥላቻ ንግግር ጋር ያለውን ግንኙነት፣ እንዲሁም የአዋጁን አስፈላጊነትና ሕገመንግሥታዊነት ይዳስሳል። በተጨማሪም እንደጥላቻ ንግግር የማይወሰዱ ንግግሮችን በተመለከተ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን ነጥቦች እና አዋጁን በተግባር በመፈፀም ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ይፈትሻል።

**ቁልፍ ቃላት፡-**

ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት፣ የጥላቻ ንግግር፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት፣ ኢትዮጵያ

## 1. መግቢያ

ሰው ከሌሎች ፍጡራን ከሚለይባቸው መሠረታዊ ነጥቦች መካከል ዋነኛው የሚያስብና የሚያመዛዝን ወይም ምክንያታዊ ፍጡር (rational/reasonable being) መሆኑ ነው።[1] የመሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች (fundamental human rights) ዋነኛ ፍልስፍናዊ

* አሮን ደጎል ሐብቱ (LLB, LLM, MBA) በቅድስት ማርያም ዩኒቨርሲቲ የሕግ እና አስተዳደር መምህር፣ ኢሜይል:- arondegol416@gmail.com
ORCID: https://orcid.org/0000-0002-6035-2222

** በብዙህ ሙሉጌታ መንክር (LLB,LLM) በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የሕግ መምህር የቀድሞ የፌደራል ዓቃቤ ሕግ፣ ኢሜይል:- bebizuh mulugeta <babimulugeta@gmail.com>
ORCID:https://orcid.org/0000-0002-5026-2282

[1] Korsgaard, Chrstine M., (2001), *Rationality*, a research paper presented to the national conference of philosophy and psychology, Delhi University, India, (Unpublished) p.1. በተጨማሪም Veatch, Henry, B. (1962), *Rational Man: A Modern Interpretation of Aristotilian Ethics*, Indiana University Press, USA, p. 17.

መሠረትም ይኸው የሰዎች ልዩ ባህርይ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ነው ሰው በተፈጥሮው ያስባል፣ በማሰላሰል አቋም ይወስዳል፣ ያሰበውንም በተለያዩ መንገዶች ለሌሎች ሰዎች ያስተላልፋል ተብሎ የሚገለጸው፡፡ በዚህም መሠረት ይህንን በተፈጥሮ ያገኘውን ስጦታና ችሎታ ይጠቀም ዘንድ ማንኛወም ሰው የሕግ ከለላ እና ጥበቃ እንደሚያስፈልገው ይታመናል፡፡ ሆኖም ግን ሰብዓዊ መብቶች በባህሪያቸው ፍፁማን ስላይደሉና የአንዱን መብት ስናከብርና ስንጠብቅ የሌሎችን መብት ወይም ጥቅም መንካት ስለሌለብን እንደሌሎቹ መብቶች ሁሉ ይህም ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ገደብ እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

በተለይም የአንድ ሰው የንግግር ነፃነት የሌላውን ሰው ክብር፣ ደህንነት ወይም ሰላም አደጋ ውስጥ የሚጥል ከሆነ ገደብ ተበጅቶለት የሁለቱን የመብትና የግዴታ ባለቤቶችን ግንኙነት ሚዛን ማስጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በዓለም አቀፍም ሆነ በአገራችን በተለያየ መልኩ የሰዎችን ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትንም ሆነ የሰዎችን መልካም ስም፣ የሕዝብን ሰላም፣ ፀጥታና ደህንነትን የሚጠብቁ ሕግጋት በተለያዩ ጊዜያት ወጥተው ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ አንዱ ነው፡፡

ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ምን ማለት እንደሆነ፣ የጥላቻ ንግግር ምንነት፣ የአዋጁ/ሕጉ አስፈላጊነት እና ተዛማጅ ጉዳዮች ወይይት የሚሹ ጭብጦች ናቸው፡፡ ይህ ጽሑፍ ለእነዚህ ጥያቄዎች ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን፣ አሥር ክፍሎች አሉት፡፡ ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ምንነትና ንድፈ ሐሳባዊ መሠረቶቹ ምን እንደሆኑ፣ ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት የሕግ ማዕቀፎች፣ በመብቱ ላይ ያሉ ገደቦች፣ ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትና በጥላቻ ንግግር መካከል ያለው ተዛምዶ፣ ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትና የጥላቻ ንግግር ሕግ በኢትዮጵያ፣ የጥላቻ ንግግር ልዩ ሁኔታዎችና ትኩረት የሚሹ አንዳንድ ነጥቦች፣ ከአዋጁ አፈጻጸም አንፃር የተቋማትና የአገልግሎት ሰጭዎች ኃላፊነት እንዲሁም የጥላቻ ንግግር ሕግና ፍርድ ቤቶች ቅጣትን በመወሰን ረገድ ያላቸው ሚና በዚህ ጽሑፍ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው ፡፡

## 2. ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ንድፈ ሐሳባዊ መሠረቶች

በአጠቃላይ ሐሳብን በነፃነት መግለጽ ሲባል ሰብዓዊ ፍጡራን በተናጠልም ሆነ በቡድን ከማንኛውም አካል ጣልቃ ገብነት ወይም ገደብ ነፃ ሆነው፣ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ሐሳባቸውን፣ እምነታቸውን ወይም ስሜታቸውን ለመግለጽ ያላቸውን ችሎታና መብት ማለት እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡[2] ይህ መብት መሠረታዊ ሰብዓዊ መብት ሆኖ ዓለምአቀፍ፣ አህጉርአቀፍና አገራዊ የሕግና ተቋማዊ ጥበቃ እንዲደረግለት ለምን አስፈለገ የሚለው ጥያቄ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህ መብት ጥበቃ ይደረግ ዘንድ ቢያንስ ሦስት ዋና ዋና ፍልስፍናዊ ሃልዮቶች (philosopical theories) ያስገድዳሉ በማለት የዘርፉ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡[3] የመጀመሪያው ሃልዮት እውነትንና እውቀትን አፈላልጎ

[2] Baker, Edwin, C. (1989), *Human Liberty and Freedom of speech*, Oxford University Press, New York, p. 6፤ በተጨማሪም Kersch, K.I. (2003), *Freedom of Speech: Rights and Liberties under the law*, ABC-CLIO, Inc., St. Barbara, California, USA, p. 13 ይመልከቱ፡፡

[3] Gedion Timotheos (2010), 'Freedom of Expression in Ethiopia: The Jurisprudential dearth', *Mizan Law Review*, Vol. 4 # 2, p. 202; በተጨማሪም Sigdel, S. (2010)', *The Cost of Reputation: Freedom of Speech and Defmation*, Unpublished (LLM Thesis), Central

ለማግኘትና ለማወቅ ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ጥበቃ ሊያገኝ ይገባዋል (freedom of expression as a prerequisite for the search for truth) ወይም (the truth theory) የተሰኘው ነው። ምክንያቱም ሓሳቦች በነፃነት ካልተንሸራሸሩና ካልተገለጹ ወይም በተለያየ መንገድ ከተለያዩ አካላት ተጽእኖና ገደብ የሚደረግባቸው ከሆነ እንኳንስ አዲስ እውነትን፣ እውቀትንና ጥበብን ለመማርና ለማወቅ ይቅርና ነባሩንም እውቀት ዳግም ለመመርመር አይቻልም በማለት በተለይም በዚህ ዙሪያ የታወቁት ሚልተንና ሚል ይሞግታሉ።[4]

ሁለተኛው ሃልዮት ከዴሞክራሲያዊ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ነፃነት (freedom of expression as a prerequisite for self-governance ወይም citizens' participation in democracy theory) ጋር የተያያዘ ነው። ከዚህ ሃልዮት ስያሜ እንደምንረዳው፣ ዜጎች የሚበጃቸውን ለመምረጥና ሓሳብን ከሓሳብ በማወዳደር፣ በቂና ምሉዕ መረጃ በመያዝ ለመወሰን ይችሉ ዘንድ የሓሳቦች በነፃነት መንሸራሸር የግድ አስፈላጊ ነው ተብሎ ይታመናል።[5] ሦስተኛው ሃልዮት (freedom of expression as a prerequisite for personal development ወይም self-fulfilment theory) የራስን ስብዕና ለማሳደግና የተሟላ፣ ነፃ የሆነና መረጃ ያለው ስብዕና እንዲኖር ለማድረግ ሓሳብን የመግለጽ መብት አስፈላጊ መሆኑን የሚገልጽ ነው። የዚህ ሃልዮት አራማጆች አንድ ሰብዓዊ ፍጡር የተሟላ ስብዕና ኖሮት ምክንያታዊና ነፃ ውሳኔ ሊወስንና ለወሰነውም ውሳኔ ሙሉ ኃላፊነት ሊወስድ የሚችለው አማራጭ ሓሳቦች ሲቀርቡለት ብቻ መሆኑን ያስረዳሉ።[6]

በአጠቃላይ ከላይ በአጭሩ እንደተገለጸው ሓሳብን በነፃነት መግለጽ ከዋነኞቹ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች መካከል አንዱ ሆኖ፣ ሕጋዊና ተቋማዊ ጥበቃና ከለላ እንዲሰጠው ማድረግ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም፣ የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጡራን ለየት ባለ መልኩ ምክንያታዊ ፍጡርና በምክንያት የሚንቀሳቀስ፣ የሚወስንና ድርጊቶችን የሚያከናውን ከመሆኑ ባሻገር፣ በየጊዜው ራሱን ለማሳደግና ስብዕናውን ለመገንባት እንዲሁም ከሌሎች መሰል አካላት ጋር ያለውን መስተጋብር በአግባቡ ለመምራት እንዲችል ሓሳብን በነፃነት መግለጽ አስፈላጊ መሆኑንን መገንዘብ ይቻላል።

---

European University, Budapest, Hungary, p. 9. በተለይም በዚህ ጽሁፍ ከተጠቀሱት ሦስቱ ዋና ዋና ሃልዮቶች (*Theories*) በተጨማሪ ሌሎችን በዝርዝር ለማየት Kersch, K.I., ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 1 የተጠቀሰውን ገጽ ከ16-26 ይመልከቱ። ከዚህ በተጨማሪም አንዳንድ ምሁራን አራት ንድፈ ሓሳቦችን ያቀርባሉ። ለምሳሌ Schauer, Frederick (1982), *Free Speech: A Philosophical Enquiry*, Cambridge University Press እና Barendt, Eric, (2007) *Freedom of Speech*, (2nd ed.,), Oxford University Press, p. 21 ይመልከቱ።

[4] Gedion Timotheos, ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 3 የተጠቀሰውን ገጽ 202 ይመልከቱ። በተጨማሪም S. Sigdel, (2010), ገጽ 11፤ እና Macleod, Christopher (Summer 2020 Edition), "John Stuart Mill", *The Stanford Encyclopedia of Philosophy*, Edward N. Zalta (ed.), URL = <https://plato.stanford.edu/archives/sum2020/entries/mill/>. (የበይነመረብ ምንጭ/Internet Source/) ይመልከቱ።

[5] Gedion Timothewos, ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 3 የተጠቀሰውን ገጽ 203 ይመልከቱ። በተጨማሪም Sigdel (2010), ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 4፣ ገጽ 16

[6] Thomas Scanlon (1972), *A Theory of Freedom of Expression*, Philosophy and Public Affairs, Vol. 1, No. 2., Princeton University Press, ገጽ 215፤ በተጨማሪም Sigdel (2010), ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 4፣ ገጽ 14 ይመልከቱ።

## 3. ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት በዓለምአቀፍ፣ አህጉር ዓቀፍና በሌሎች አገራት ሕግጋት ያለው ቦታ

ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት በዓለም ደረጃ ረዘም ያለ ታሪክ ያለውና ሰፊ ትግል የተደረገበት መሠረታዊ ሰብዓዊ መብት ነው። የመብቱን ይዘት፣ አስፈላጊነትና ሊደረግለት የሚገባውን የሕግ ጥበቃ በማስመልከት ብዙ ተጽፏል። ከዚህም በተጨማሪ ይህን መብት በሚመለከት በርካታ ዓለም አቀፋዊ የሕግ ሰነዶች ፀድቀዋል። በዓለምአቀፍ ደረጃ ለዚህ ሰብዓዊ መብት ዕውቅና በመስጠት ሕጋዊ ጥበቃ ያደረገው ሰነድ ሁሉን አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (1948 እ.ኤ.አ) /Universal Declaration of Human rights (UDHR) / ነው። ይህ ሰነድ በአንቀጽ 19፦

> ማንም ሰው አስተያየት የመስጠትና ሓሳቡን የመግለጽ ነፃነትና መብት አለው። ይህ መብት እያንዳንዱ ሰው ያለምንም ተጽእኖ አስተያየት እንዲኖረውና ጠረፍ ሳይወስነው በማናቸውም ዓይነት መሣሪያ መረጃዎችና ሓሳቦችን የመፈለግ፣ የመቀበልና የማስተላለፍ ነፃነትን ይጨምራል፤

በማለት ይደነግጋል።

ሌላው ዐብይ ሰነድ (እ.ኤ.አ) በ1966 የወጣውና አገራት ላይ ግልጽ በሆነ መልኩ ሕጋዊና ሞራላዊ ግዴታ የሚጥለው ዓለምአቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች የቃል ኪዳን ስምምነት ነው። በዚህ ስምምነት አንቀጽ 19 መሠረት፦

1. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የራሱ አስተያየት ሊኖረው መብት አለው፤
2. ማንኛውም ሰው ሓሳብን የመግለጽ ነፃነት አለው። ይህም መብት መረጃና ማንኛውንም ዓይነት ሓሳብ ያለምንም የድንበር ገደብ፣ የመፈለግ፣ የማግኘትና በቃል፣ በጽሑፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ-ጥበብ ወይም ሌላ በመረጠው ዘዴ የማስተላለፍ መብትን ያጠቃልላል፣
3. [በአንቀጽ 19] ንዑስ ቁጥር 2 የተደነገጉትን መብቶች አጠቃቀም ሁኔታ ልዩ ግዴታዎችንና ኃላፊነቶችንም አብሮ ይዟል፤ በዚህም ምክንያት የተወሰኑ ገደቦች ሊደረጉበት ይቻላል፣ ይሁን እንጂ ገደቦቹ በሕግ የተደነገጉና ፡
   (ሀ) ሌሎችን መብቶችና ክብር ለማስጠበቅ
   (ለ) የብሔራዊ ፀጥታን፣ የሕዝብን ደህንነት፣ ወይም ጤናን ወይም ሥነምግባርን ለማስከበር አስፈላጊ መሆን አለባቸው።

ከዚህም በተጨማሪ የዚሁ የቃል ኪዳን ስምምነት ሰነድ አንቀጽ 20 ማንኛውንም የጦርነት ፕሮፓጋንዳም ሆነ ጥቃትን የሚያነሳሳ የዘር፣ የብሔር ወይም ኃይማኖታዊ ጥላቻን መስበክ በሕግ የተከለከለ መሆኑን ይደነግጋል። ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትን በተመለከተ፣ ይህ ስምምነት ከላይ ከተጠቀሰው ከ1948 (እ.ኤ.አ) ሁሉ አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ጋር በይዘት ተመሳሳይነት አለው። የመግለጫው አንቀጽ 29(2) ላይ ይህንኑ መብት ጨምሮ በሌሎች መብቶች ላይ ያሉ ገደቦችን ጠቅለል ባለ አገላለጽ ያሳያል። ይህ ድንጋጌ አጠቃላይ የመብት ገደቦች ድንጋጌ (General Limitation Clause) ተብሎ ይጠራል። በተጨማሪም መብቱን ከማክበርና እውቅና ከመስጠት አልፎ መብቱ ሊገደብ የሚችልበትን ልዩ ሁኔታዎችም ስምምነቱ ያሳያል።

በአህጉራችን በአፍሪካም (እ.ኤ.አ) በ1981 የወጣውና የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር (African Charter on Human and People's Rights/ACHPR/) በመባል የሚታወቀው የሕግ ሰነድ (አንቀጽ 9) ለዚህ መብት ጥበቃ ሰጥቷል። ቻርተሩን የተቀበሉ አገራት ይህን መብት ጨምሮ ሌሎች በቻርተሩ የተካተቱት መብቶችና ነፃነቶች

መከበራቸውን የማረጋገጥ ግዴታ እንዳለባቸው በአንቀጽ 25 ተደንግጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣

- በ1950 (እ.ኤ.አ) በወጣው የአውሮፓው የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት (European Convention for the Protection of Human Rights and Fundamental Freedoms/ECHR/ አንቀጽ 10)፣
- በደቡብ አሜሪካ አገራት፣ እ.ኤ.አ በ1969 በወጣው የአሜሪካው የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት (Inter-American Human Rights Convention/ አንቀጽ 13)፣ እና
- እ.ኤ.አ በ1948 በወጣው የአሜሪካ የሰው ልጆች መብትና ግዴታ መግለጫ (American Declaration on the Rights of Man)

ይህ መሠረታዊ የሰው ልጆች መብት ሰፊ እውቅናና የሕግ ጠበቃ ተደርጎለታል፡፡ በሌሎች አገራትም ይኸው መብት ጥበቃ የተደረገለት መሆኑንን ከብዙ ጽሑፎችና ሕግጋተ መንግሥቶቻቸው ማወቅ ይቻላል፡፡[7]

እነዚህ ዓለምአቀፍ የሕግ ማዕቀፎችና የአገራት ልምዶች የሚያሳዩት በአንድ አገር የዳበረ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዕድገትና ብልጽግና ሊኖር የሚችለው ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት በአግባቡ ሲከበር መሆኑን ነው፡፡ ያም ሆኖ፣ ብዙዎች እንደሚስማሙት፣ ይህ መብት ምንም እንኳ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብት ቢሆንምና ከዓለምአቀፍና አህጉር አቀፍ ሕግጋት እስከ አገራዊ ሕግጋተ መንግሥታት ድረስ ጥበቃ የተደረገለት መሆኑ ግልጽ ቢሆንም፣ ፍፁማዊና ገደብ የለሽ መብት ነው ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በመሠረቱ ማንኛውም ሰብዓዊ መብት ፍፁማዊ መብት ሳይሆን የሌሎችን ሰዎች መብትና ጥቅም፣ አገራዊ ደህንነትና የሕዝብ ሰላም እንዲሁም ሞራላዊ ጉዳዮችን ባገናዘበ መልኩ ገደቦች ሊጣሉ እንደሚችሉ ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡[8] ከነዚህም መካከል አንዱ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ ወሬዎችን ማሰራጨት ሲሆን ይህ ገደብ ከዋናው ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ጋር እንዴት መታየት እንዳለበት ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

---

[7] ለምሳሌ ህንድ በ1982፣ ደቡብ ኮሪያ በ1989፣ ደቡብ አፍሪካ በ1996፣ ታይላንድ በ1997፣ ጃፓን በ2001 እንዲሁም ስዊድን በ1766 (ሁሉም እ.ኤ.አ ናቸው) ሕግጋተ መንሥቶቻቸውና ሕጎቻቸው ውስጥ ለዚህ መሠረታዊ የሰው ልጆች መብት ጥበቃ አድርገዋል፡፡[7] በአሜሪካም ምንም እንኳ እ.ኤ.አ በ1787 ሕገ መንግሥት ላይ ስለ ንግግር ወይም ሓሳብን በነፃነት መግለጽ የተባለ ነገር ባይኖርም እ.ኤ.አ በ1791 በፀደቀውና በመጀመሪያው የሕገ መንግሥታቸው ማሻሻያ (1st amendement of 1791) ተብሎ በሚጠራው የማሻሻያ ሰነድ ላይ ሕግ አውጭው ምክር ቤት ሓሳብን በነፃነት የመግለጽና የፕሬስ መብትን የሚገድብ ሕግ ማውጣት እንደሌለበት ተደንግጓል፡፡ "…Congress shall make no law abridging the freedom of speech or of the Press …". በመሠረቱ በአገረ አሜሪካ እ.ኤ.አ እስከ 1920ዎቹ ድረስ ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት እንደ አደገኛ ሓሳብ ነበር የሚታየው፡፡ ከዚያም በኂላ ለመጀመሪያ ጊዜ እ.ኤ.አ በ1930ዎቹ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህ መብት ጥበቃ ያስፈልገዋል የሚል አቋም ያዘ፡፡ Samuel Walker, 'Hate Speech: The History of American Controversy', cited in Bell, Jeannine, (2009), 'Restraining the Heartless: Racsist speech and Minority Rights', *Indiana Law Journal*, Vol. 84 issue 3, p. 968. በተጨማሪም፣ Michael Rosenfield (2003), 'Hate Speech in Constitutional Jurisprudence: A Comparative Analysis', *Cardozo Law Review*, Vol. Vol. 24 # 4 ገጽ 1529 መመልከት ይቻላል፡፡

[8] Wojciech Sadurski (1999), *Freedom of Speech and its Limits,* Kulwer Academic publishers, ገጽ 179፤ በተጨማሪም *The Article 19 Freedom of Expression handbook, International and Comparative law, standards and procedures*, (1993), ገጽ 114 እና Cram, Ian, (2006), *Contested words: Legal Restrictions on freedom of speech in Liberal democracies*, Ashagate publishing limited, England, ገጽ 97 መመልከት ይቻላል፡፡

## 4. ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ ያሉ ገደቦች መርህ

> "እጄን ወደፈለግኩበት አቅጣጫ ማወናጨፍ እችላለሁ፣ የእርስዎን አፍንጫ እስካልነካሁ ድረስ" ("I have the right to stretch my hands so long as I don't touch your nose.")

ሐሳብን በነፃነት መግለጽ ፍፁማዊ መብት ሳይሆን የራሱ የሆኑ ገደቦች ያሉት መሆኑን ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነት ሰነዶች ያሳያሉ። በመብቱ አጠቃቀም ላይ እነዚህን ገደቦች ማድረግ ለምን እንደተፈለገና በምን መልኩ ሊቀረጽ እንደሚገባው የተባበሩት መንግሥታት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች የቃል ኪዳን ስምምነትን አፈጻጸም ለመከታተል የተቋቋመው የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ አጠቃላይ ትርጉም ቁ. 34 (General Comment # 34) መስፈርቶችን አስቀምጧል።[9] የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ አጠቃላይ ትርጉም ቁ. 34 (General Comment # 34) የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚቴ በሰኔ ወር 1983 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) አውጥቶት የነበረውን አጠቃላይ ትርጉም ቁ. 10 (General Comment # 10) የተካ ነው።

### 4.1 የሕጋዊነት መርህና የምክንያታዊ ተቀባይነት መርህ

ሐሰብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ ገደብ ለማድረግ የሚጠቀሰው የመጀመሪያው መርህ *የሕጋዊነት መርህ* (the *principle of legality*) ነው። እ.ኤ.አ በ1966 ዓ.ም የወጣው ዓለምአቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች የቃል ኪዳን ስምምነት (ICCPR) አንቀጽ 19(3) ላይ ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ የሚጣሉ ገደቦች በሕግ የተደነገጉ መሆን እንዳለባቸው ያስገድዳል። ይህም ማለት ግልጽና በአገሪቱ የሕግ አወጣጥ ሥርዓት መሠረት ሕግ ሳይወጣ በአስፈጻሚው አካል ወይም በአሠራር ደረጃ ይህንን መሠረታዊና ሕገ መንግሥታዊ መብትን መገደብም ሆነ አፈጻጸሙን መክልከል ተገቢ አይሆንም። ሁለተኛው መስፈርት ደግሞ *ምክንያታዊ ተቀባይነት መርህ* (the *principle of legitimate aim*) በመባል ይታወቃል። ይህም በዓለምአቀፉ ስምምነት አንቀጽ 19(3) መሠረት፣

- የሌሎች ሰዎችን መብት ለመጠበቅ
- ብሔራዊ ጸጥታና አገራዊ ደህንነትን ከአደጋ ለመከላከል
- የሕዝብ ሰላም፣ ሞራልንና ጤናን ለመጠበቅ

ገደብ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው።

በእነዚህ ምክንያቶች መነሻ የሚደረግ ገደብ ምክንያታዊና በማንኛውም መልኩ ተቀባይነት አለው ተብሎ ይታመናል። *የሌሎችን መብት መጠበቅ ሲባል*፣ ማንም ሰው ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት መጠቀምን ምክንያት በማድረግ የሌሎችን ሰዎች ክብር፣ የኃይማኖት ሥርዓት፣ ብሔር ወይም ማንኛውንም ዓይነት ስብዕናን በሚነካ መልኩ የመንካትና የመድፈር ተግባር እንዳያከናውን ማድረግ ነው፤ የእነዚህ አካላት መብት የሚጀምርበት ድንበር የግለሰቡ መብት የሚያበቃበት እንደሆነ ማወቅ ይገባል።

[9] Human Rights Committee, General Comment # 34: Freedom of Expression (Art. 19) 29/06/83, Para. 4. በተጨማሪ Yonas Birmeta, (2008), 'Freedom of Expression and Crimes Against Honor Under Ethiopian Law: An Assessement of their compatability' in Girmachew A. and Sisay A. (Eds), 'The Constituional Protection of Human rights in Ethiopia Chalenges and Prospects', *Ethiopian Human Rights Law Series*, Vol. 2, AAU, Faculty of Law ገጽ 106

*ብሔራዊ ፀጥታንና አገራዊ ደህንነትን* ከአደጋ ለመከላከል እንዲሁም አገራዊ ደህንነትን ለመጠበቅ ሲባል የአገርን ምስጢር ወይም ማንኛውንም አገራዊ መረጃ ወይም ማንኛውንም የአገሪቱን ጸጥታና ውጫዊም ሆነ ውስጣዊ ድህንነት አደጋ ላይ የሚጥል መረጃ ማውጣት ወይም ይፋ ማድረግ ወይም በዚህ ረገድ ማንኛውንም ትችት መሰንዘር ሓሳብን በነፃነት መግለጽ ነው ሊባል አይችልም፡፡[10]

አንድ አገር ውስጥ የሚገኝ ሕዝብ ሉዓላዊ እንደመሆኑ መጠን የራሱ የሆኑ የባህል፣ ሞራልና ሕብረተሰባዊ እሴቶች፣ መርሆችና መስፈርቶች ያሉት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚህ *ሞራላዊ፣ ባህላዊና ሕብረተሰባዊ እሴትና መስፈርት* ባፈነገጠ ሁኔታ ሓሳብን በነፃነት መግለጽ በሚል፣ ከማኅበረሰቡ እሴትና መርህ የሚጣረስ ተግባር ወይም የእሴቱን ክብርና ደረጃ በሚያዋርድ ወይም ዝቅ በሚያደርግ መልኩ ሓሳብን መግለጽ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

በመሠረቱ ሕብረተሰባዊ ሞራልና እሴት ማለት ምን ማለት ነው? መለኪያና መስፈርቶቹስ ምንድናቸው? የሚለው ጥያቄ አወዛጋቢና የተለያዩ ምላሾችን የያዘ ነው፡፡ ምክንያቱም ሞራላዊ ጉዳይ ሁሉንም ሊያስማማ የሚችል ወጥ የሆነ መለኪያ መስፈርት ያለው ሳይሆን እንደየአገሩ ባህል፣ የእድገትና አስተሳሰብ ደረጃና ሥልጣኔ የሚታይ ነው፡፡ በአብዛኛው በዚህ ውስጥ የሚጠቃለሉ ጉዳዮች ወሲብ ነክ የሆኑ (pornography) እና ኃይማኖታዊ ጽርፈት (ስድብና ክብርን መንካት) (blasphemy) ተብለው የሚጠሩት ናቸው፡፡[11] ከዚህ በተጨማሪም የሚጣለው ገደብ የሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍሎች ባህላዊና ኃይማኖታዊ እሴትና አስተሳሰብን ጥበቃ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ እንጂ የአንድን ወገን ባህላዊ፣ ሞራላዊ ወይም ኃይማኖታዊ እሴት በሌሎቹ ላይ ገደብ ለመጣል እንደመለኪያ ሊወሰድ አይገባም የሚል ዓለምአቀፍ አስተሳሰብ አለ፡፡[12]

የሕዝብ *ሰላምና ጤናን ለመጠበቅ* የሚለው ሌላው ምክንያታዊ ተቀባይነት ያለው ገደብ ሲሆን፣ ሓሳብን በነፃነት መግለጽ በሚል የጦርነት ቅስቀሳ ማድረግ፣ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር የሚያጋጭ ወይም ጠብን የሚዘራ ወይም አላስፈላጊ በቀልን የሚያነሳሳ ገለፃ ማድረግ የወንጀል ድርጊት ነው፡፡ የሕዝብ ጤናንም በሚመለከት፣ በተመሳሳይ መልኩ ለምሳሌ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተብለው የሚታወቁት እንደ የሴት ልጅ ግርዛትን ማስተዋወቅና ማበረታታት፣ ከጥሎሽ ዕዳ ጋር የተያያዙ አገላለጾች ወይም በሌሎች በተለይም በደቡባዊ ምሥራቅ እስያ አገሮች ቦታዎች እንደ ባህል የሚወሰዱ አሰቃቂ ድርጊቶችን እንደ ባህላዊ እሴት ወስዶ በይፋ መግለጽ ወይም ማበረታታት ተቀባይነት የሌለውና ሓሳብን በነፃነት ከመግለጽ መብት ጽንሰ ሓሳብ ጋር የሚጋጭ ድርጊት ነው፡፡[13]

### 4.2 የዲሞክራሲያዊ አስፈላጊነት መርህና እና የተመጣጣኝነት መርህ

ሦስተኛው መርህ *ዴሞክራሲያዊ አስፈላጊነት* (the *principle of democratic necessity*) ተብሎ ይጠራል፡፡ ሓሳብን በነፃነት መግለጽ መሠረታዊ መብት እንደመሆኑ፣

---

[10] Yonas Birmeta, (2008), ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 9 የተጠቀሰውን ገጽ 109 ይመልከቱ፡፡ በተጨማሪም Toby Mendel (2003), *The Johanesberg Principles: Overview and implementation*, ገጽ 8 ይመልከቱ፡፡

[11] ዝኒ ከማሁ ገጽ 111

[12] United Nations Human rights Committee General Comment # 30th of July 1993, p. 3.

[13] Yonas Birmeta, (2008), ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 10 የተጠቀሰውን ገጽ 109 ይመልከቱ፡፡ በተጨማሪም Mendel, Toby, (2003), The Johanesberg Principles: Overview and implementation, ገጽ 8 ይመልከቱ፡፡

በዚህ መርህ መሠረት ገደብ ሊጣልበት የሚገባው ለዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ግንባታ አስፈላጊ መሆኑ ሲታመን ብቻ ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ አስፈላጊነት ሲባል ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት አስፈላጊ መሆኑን ሲያምንበት ነው ማለት ሳይሆን እንደ አጠቃላይ ዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ገደቡ አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበት ነው፡፡[14]

በተለይም የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ፍርድ ቤት በሰጠው ትርጉም መሠረት ገደቡ ሊጣል ወይም መብቱ ሊገደብ የሚችለው መንግሥት ያወጣውን ገዳቢ ሕግ ብቻ መሠረት በማድረግ ወይም መንግሥት እንዲሁ ስላመነበት ሳይሆን እጅግ በጣም በጠባቡ መተርጎም በሚቻልበት ሁኔታ መሆን አለበት፡፡[15] ዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ሲባል ግልጽነት፣ አሳታፊነትና ብዝሃነት ያለበት የመቻቻል ባህል የሰፈነበትና የአስተሳሰብና አመለካከት ደረጃው ከፍ ያለ ማኅበረሰብ ማለት ነው፡፡[16] በተለይም የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ አጠቃላይ ትርጉም ቁ. 34 (General Comment # 34) ዴሞክራሲያዊ አስፈላጊነት (necessity) የሚለውን መርህ በተብራራ ሁኔታ በመግለጽ፣ ከሰነዱ መውጣት በፊት ኮሚቴው ያስተናገዳቸውን የአገራት ጉዳዮችና የተገነዘባቸውን ድምዳሜዎች (concluding observations) በማብራሪያነት እንደማሳያ ተጠቅሟል፡፡[17]

አራተኛው እና የመጨረሻው መርህ *የተመጣጣኝነት መርህ* (*principle of proportionality/balancing*) የሚባለው ነው፡፡ ስለመርሁ ምንነትና ይዘት በርካታ ምሁራን የተለያየ ትንታኔ ሰጥተዋል፡፡ ለምሳሌ፣ የካናዳ ጠቅላይ ፍርድ ቤት (እ.ኤ.አ) በ1986 ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ ከሚጣሉት ገደቦች አንዱ የተመጣጣኝነት መርህን የተከተለ መሆን እንዳለበት ትንታኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትንታኔ መሠረት መብቱን በመገደብ (ወይም መብቱ ላይ ገደብ በማስቀመጥ) ማሳካት በተፈለገው ዓላማና ግብ እና በሚጣለው የገደብ መጠን መካከል መጣጣም ወይም ሚዛኑን መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ የተለየ አገላለጽ በመጠቀም፣ ሌሎች አገሮችም ይህንኑ የተመጣጣኝነት/ ሚዛናዊነት መርህ ይቀበላሉ፡፡ በአጠቃላይ አነጋገር፣ ይህ መርህ የመብቱ ባለቤትና ተጠቃሚ በሆነው ሰው ነፃነት እና በኅብረተሰቡ ጥቅምና ደህንነት መካከል፣ መብቱን በመጠቀም ዙሪያ ሚዛኑ የተጠበቀ መሆን አለበት የሚል ሓሳብ የያዘ ነው፡፡[18]

## 5. የጥላቻ ንግግርና ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት

ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ሊጠበቅና ሊከበር የሚገባው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እንደሌሎቹ ሰብዓዊ መብቶች ሁሉ፣ ይህም መብት ፍፁማዊ ሳይሆን ገደብ ያለበት ነው፡፡ በሰብዓዊ መብት አራማጅነት ከሚታወቁት አንዱ የሆነው ጆን ሎክ እንደገለፀው፣ ፍፁማዊ መብት ወይም ፍፁማዊ ነፃነት የሚባል ነገር የለም፤ ፍፁማዊ መብት ወይም ፍፁማዊ ነፃነት የመብትን ጽንሰ ሓሳብ ራሱኑ ያጠፋዋልና ("There is no such thing

---

[14] ዝኒ ከማሁ ገጽ 111

[15] In the matter of *Lohe Issa Konate Vs. Burkina Faso*, application number 004/2013, African Court on Human and Peoples Rights, pp. 19-20.

[16] ዝኒ ከማሁ

[17] United Nations Human Rights Committee General Comment # 34 of 29th July 2011 p. 9.

[18] Gregoire Webber (2019), 'Proportionality and limitations on Freedom of Speech', *Queen's Law Research Paper Series*, p. 13.

as absolute freedom as absolute freedom destroys the concept of freedom itself”)።[19]

### 5.1 የሌሎች ሰዎችን መብትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ

አንድ ሰው ሓሳቡን በነፃነት የመግለጽ መብቱን ሲጠቀም ወይም ተግባር ላይ ሲያውል የሌሎችን ሰዎች ነፃነት፣ ክብር፣ ደህንነትና አጠቃላይ መብትን ባከበረና በጠበቀ መልኩ መሆን መቻል አለበት። ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት በመጠቀም ስም የሌሎችን ሰዎች መብት የሚጥስ ወይም የሚጋፋ ከሆነ፣ ይህ ድርጊት በመብት የመጠቀም ተግባር ሳይሆን የመብት ጥሰት ይሆናል ማለት ነው። የጥላቻ ንግግር ክልከላ (prohibition of hate speech) ከነዚህ ገደቦች መካከል አንዱ ነው።

በዓለም አቀፍም ሆነ በአህጉር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች ስምምነት ሕጋዊ ሰነዶች ላይ እንደተጠቀሰው፣ ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ገደቦች አሉት። ከላይ በተራ ቁጥር 4.1 በአጭሩ እንደተመለከተው፣ ከእነዚህ ገደቦች መካከል የሌሎችን መብቶችና ክብር ለማስጠበቅና የብሔራዊ ጸጥታን፣ የሕዝብን ደህንነት፣ ወይም ጤናን ወይም ሥነ ምግባርን የማስጠበቅ ዓላማዎችን እናገኛለን። ከነዚህ ጠቅላላ የሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች ዓለምአቀፍ ሕጋዊ የስምምነት ሰነዶች በተጨማሪ ለምሳሌ የዘር መድልዎን ለማስወገድ በ1965 እ.ኤ.አ የተፈረመው ስምምነት (International Convention on the Elimination of all Forms of Racial Discrimination (ICERD))፣ አንቀጽ 4፣ የስምምነቱ ፈራሚ አገራት ያንዱን ዘር ወይም አንድ ዓይነት ቀለም ወይም ጎሳ ያላቸውን ሰዎች የበላይነት በሚያንፀባርቅ ትምህርትና ንድፈ ሓሳብ ላይ የተመሠረተ ፕሮፓጋንዳ ማራመድና የዘር ልዩነትን ማነሳሳት እንደማይችሉ ይደነግጋል። ከዚሁ ጋር የተያያዙ ተግባራትን ለማስቀረት ተገቢውን እርምጃ ባፋጠኝ ለመውሰድ መስማማታቸውንም ይገልፃል።

የጥላቻ ንግግር በአገራት ሰላም እና መረጋጋት እንዲሁም በሰው ልጆች ደህንነት ላይ ባስከተለው እና በሚያስከትለው ከፍተኛ አደጋ ምክንያት፣ ይህንን ድርጊት ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ሓሳብን በነፃነት በመግለጽ መብት ላይ ገደቦች ማድረግ አስፈላጊ ስለመሆኑ የሚከራከሩ ወገኖች አሉ።[20] በሌላ በኩል ስለጥላቻ ንግግር ምንነት የሕግ ትርጓሜ ለመስጠት የሚደረገው ጥረት በሌሎች የሕግ ጥበቃና እውቅና ባገኙ ሰብዓዊ መብቶች ላይ አላስፈላጊ የሆነ ጫና የሚፈጥር መሆኑን በማንሳት የሕጎችን መውጣት የሚቃወሙ አሉ።[21] የጥላቻ ንግግርን ለመቆጣጠር በሚወጡ ሕጎች ውስጥ የጎንዮሽ ጉዳት ይደርስባቸዋል ተብለው ከሚታሰቡት ሰብዓዊ መብቶች ውስጥ ሓሳብን በነፃነት

---

[19] በእርግጥ ለዚህ አባባል አንዳንድ በስተቀሮች (ልዩ ሁኔታዎች) እንዳሉት ግልጽ መሆን አለበት። ለምሳሌ ከኢሰብዓዊ አያያዝ የመጠበቅ መብት፣ የባርነት ክልከላ እንዲሁም የሕጻናት በሕይወት የመኖር መብት ፍፁማዊ መብቶች ሲሆኑ ምንም ዓይነት ገደብም ሆነ ልዩ ሁኔታ ሊቀመጥላቸው አይችልም።

[20] Andrea Schefler (2015) *The Inherent Dangers of Hate Speech Legislation*: A case study from Rwanda and Kenya on the Failure of a Preventive measures, (fesmedia Africa, Friedrich-Ebert-Stiftung), pp. 9-10;
Available at: https://library.fes.de/pdf-files/bueros/africa-media/12462.pdf;
Henry Maina, *The Prohibition of Incitement to Hatred in Africa*: *Comparative Review and Proposal for a Threshold*, A Study Prepared *for* the Regional Expert Meeting on Article 20, Organized by the Office of the High Commissioner for Human Rights, Nairobi, (April 6-7, 2011).

[21] ዝኒ ከማሁ

የመግለጽ መብት እና ኃይማኖትን የማራመድ መብቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በዚሁ ምክንያትም የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በሚወጡ ሕጎች፣ እነዚህን ስጋቶችና በሌሎች መብቶች ላይ የሚያስከትሉትን ጫና ለማስቀረት እንደ ጥላቻ ንግግር የማይወሰዱ ንግግሮች/ድርጊቶች በልዩ ሁኔታነት ተካተው ይገኛሉ፡፡

## 5.2 የጥላቻ ንግግር መገለጫዎች

**የጥላቻ ንግግር** በግልጽ በሕግ ክልከላ ሊደረግበት በሚችል መልኩ ሳይሆን ሊያስከትለው ከሚችላቸው ጉዳቶችና አጠቃላይ ሁኔታዎች አንፃር ልንገነዘበው እንደሚገባ አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡[22] በሌላ በኩል ደግሞ፣ ይህ ድርጊት በግልጽ ሕገ ወጥ በሆነ መልኩ ሊታገድ እንደሚገባና ሕግ አውጭውም ሆነ ፍርድ ቤቶች ጠንከር ያለ ገደብ ሊጥሉበት በሚችል መልኩ መወሰድ አለበት በማለት አጥብቀው የሚከራከሩ አሉ፡፡[23] ከሁለቱ አመለካከቶች የተለየ አቋም ያላቸው ጸሐፊዎች ደግሞ ድርጊቱ በሕግ ክልከላ ሊደረግበት የሚገባ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕጉን ማስፈጸም ወይም በተግባር ላይ ማዋል ግን እንደመጨረሻ አማራጭ መወሰድ እንዳለበት ያምናሉ፡፡[24]

ለምሳሌ ያህል በአንድ ጽሑፍ፣ የጥላቻ ንግግር ማለት የአንድን ማኅበረሰብ ክብር በሚነካ መልኩ የዚያን ማኅበረሰብ ኃይማኖት፣ ብሔር ወይም ዘር ማጥላላትና ማኅበረሰቡ ጥቃት እንዲደርስበት ወይም እንዲገለል ወይም መድሎ እንዲደርስበት ማነሳሳት ማለት ነው፣ የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡[25] የተባበሩት መንግሥታት የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል ባወጣው ስትራቴጂና የድርጊት መርሀ ግብር ሰነድ ላይም የጥላቻ ንግግር ማለት በቃል፣ በጽሑፍ ወይም በሌላ አኳኋን የአንድን ሰው ወይም ቡድን ብሔር፣ ኃይማኖት፣ ጾታ፣ ቀለም፣ ዜግነት ወይም ሌላ ማንኛውንም ማንነትን መሠረት ያደረገ እና የዚያን ሰው ወይም ቡድን መልካም ስምና ክብር ያዋረደ፣ ዝቅ ያደረገ ንግግር ማለት ነው የሚል ትርጉም ተሰጥቶት እናገኛለን፡፡[26]

---

[22] Calvin R. Massey (1992), 'Hate Speech, Cultural Diversity, and the Foundational Paradigms of Free Expression', 40 *UCLA L. Rev*. 103 ገጽ 155

[23] Mari J. Matsuda (1989), 'Public Response to Racsist Speech: Considering the Victims Story', *Michigan Law Review*, ገጽ 2380

[24] Bhikhu Parekh, 'Is There a Case for Banning Hate Speech?' Cited in Sellars, F. Andrew, (2016), *Defining Hate Speech*, Research Publication No. 2016-20, The Berkman Klein Center for Internet & Society Research Publication Series: The Social Science Research Network Electronic Paper Collection, Boston University School of Law, Public Law Research paper ገጽ 14 15

[25] "… hate speech constitutes denigration of the reputation of a social group, stereotyped by some particular national, racial or religious characteristics, accompanied by incitement to hostility, violence and discrimination against that group"
Fabio Maneli, *Repression of hate speech: its foundation in international and European law in Hate Crime and Hate speech in Europe: Comprehensive analysis of International law principles*, Eu-wide study and national assessements, PRISM Research Project, ገጽ 11

[26] United Nations Strategy and Plan of Action on Hate Speech, A Synopsis, May, 2019, p. 2

በተመሳሳይ መልኩ የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽ/ቤት (እ.ኤ.አ) በ2013 ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ እና ጥላቻ ማነሳሳትን በተመለከተ ያወጣውና የራባት የድርጊት መርሀ ግብር (Rabat Plan of Action) በመባል የሚታወቀው ሰነድ አንድን ንግግር ጥላቻ አዘል ነው ለማለት ቢያንስ ስድስት ነጥቦች መታየት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ *የመጀመሪያው መስፈርት አውድ* (context) ሲሆን፣ አንድ መልዕክት ኢላማ በተደረገ ቡድን ላይ አድልዎ፣ ጠላትነት ወይም ጥቃትን ማነሳሳት መቻሉን ለመመዘን የንግግሩን ድርጊት ንግግሩ በተደረገበትና በተሰራጨበት ወቅት በነበረው ማኅበራዊና ፖለቲካዊ አውድ ውስጥ አስገብቶ ማሳየትን የሚሻ ነው፡፡

*ሁለተኛው መስፈርት ተናጋሪው* (speaker) ነው፡፡ ይህም ሲባል ተናጋሪው በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው ቦታ ወይም ደረጃ፣ በተለይም የግለሰቡ ወይም ድርጅቱ አቋም የንግግሩ ኢላማ በሆነው የአድማጭ አውድ ውስጥ ታሳቢ መደረግ አለበት፡፡ *ሦስተኛው መስፈርት ደግሞ ዓላማ* (intent) ሲሆን ቸልተኝነትና ግድየለሽነት አንድን ድርጊት በዓለም አቀፉ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች የቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 20 መሠረት የወንጀል ድርጊት ለማስባል በቂ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ይህ አንቀጽ አንድን ንግግር ወይም መልእክት ከማሰራጨት ይልቅ ማነሳሳት ወይም ቅስቀሳ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በዚህ ረገድ በንግግሩ ባለቤትና ፍሬ ነገር እንደዚሁም በአድማጩ መካከል የሦስትዮሽ ግንኙነት መኖርን ይጠይቃል፡፡

*አራተኛው መስፈርት ይዘትና ቅርጽ* (content) ሲሆን የንግግሩ ይዘት በፍርድ ቤት ክርክር ሂደት ዐበይት ትኩረት ከሚደረግባቸው ጉዳዮች አንዱ የሆነና የማነሳሳት ድርጊት ወሳኝ መገለጫ ነው፡፡ የይዘት ትንተና ንግግሩ ያለውን የጠብ አጫሪነትና የቀጥተኛነትን ደረጃ፣ እንደዚሁም የንግግሩ ቅርጽ፣ ዘይቤና ተፈጥሮ፣ የተነሳውን ክርክር ሁኔታ፣ ወይም ጥቅም ላይ በዋሉት ክርክሮች መካከል የተፈጠረውን ሚዛን ሊያካትት ይችላል፡፡ *አምስተኛው* ነጥብ የንግግር ተግባር *መጠን* (extent) ሲሆን የንግግሩ ተግባር የሚደርስበትን ማዕቀፍ፣ ሕዝባዊ ተፈጥሮውን፣ የንግግሩን ግዝፈትና የአድማጩን መጠን ያካትታል፡፡ በራባት የድርጊት መርሀ ግብር ስለጥላቻ ማነሳሳት የተገለፀው *ስድስተኛ* ነጥብ *የጉዳቱ ሊይቀሬነት* (likelihood of harm) የሚል ነው፡፡

አንድ ንግግር በወንጀል እንዲፈረጅ በማነሳሳት ንግግር ቅስቀሳ የተደረገበት ድርጊት የግድ ወዲያውኑ መፈጸም የለበትም፡፡ ይሁን እንጂ የተወሰነ የጉዳት ስጋት (likelihood) መታየት አለበት፡፡ ይህም ማለት ኢላማ በተደረገው ቡድን ላይ ተጨባጭ ጥቃት እንዲካሄድ በማነሳሳት ረገድ የጥላቻ ንግግሩ ስኬታማ ሊሆን የሚችልበት ምክንያታዊ የሆነ ዕድል እንደነበረው ፍርድ ቤቶች መወሰን ይኖርባቸዋል ማለት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ቀጥተኛ የሆነ መንስኤ መኖር ይኖርበታል፡፡[27]

### 5.3 የጥላቻ ንግግር ትርጉምና ታሪካዊ ዳራ

እ.ኤ.አ በ1986 የወጣው የሀገረ እንግሊዝ፣ ስኮትላንድና ዌልስ ፐብሊክ ኦርደር አክት (Public Order Act of 1986) ተብሎ የሚታወቀው ሕግ በማናቸውም የተወሰኑ ሰዎች ወይም ቡድኖች ላይ ጥላቻንና መገለልን የሚያስከትል፣ ዘረኝነትን የሚያበረታታ ንግግር የጥላቻ ንግግር ተብሎ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡[28] በእኛም አገር የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ

---

[27] The UN High Commisioner for Human Rights, The Rabat Plan of Action on the Freedom of Expression Vs. Incitement to hatred, 2013.

[28] Sec. 18 of the Public Order Act of England, Scotland and Wales.

መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1185/2012 ለጥላቻ ንግግር ትርጉም ሰጥቷል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 2(1) ንግግር የሚደረግበት መንገድ (means) "በቃል፣ በጽሑፍ፣ በምሥልና ሥዕል፣ በቅርጻ ቅርጽና በሌሎች ተመሳሳይ መንገዶች በመጠቀም" እንደሆነ ይገልፃል፡፡ በይዘት (content) ረገድ ደግሞ፣ የጥላቻ ንግግር "በአንድ ሰው ወይም በተወሰነ ቡድን ማንነት ላይ ያነጣጠረ፣ ብሔርን፣ ብሔረሰብንና ሕዝብን፣ ኃይማኖትን፤ ዘርን፣ ጾታን ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሠረት በማድረግ ሆን ተብሎ ጥላቻን፣ መድሎን ወይም ጥቃትን የሚያነሳሳ ንግግር" ማለት እንደሆነ በአንቀጽ 2(2) መሠረት ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም፣ የጥላቻ ንግግር ማለት በይፋ የአንድን ግለሰብ ወይም ቡድን ብሔር፣ ወዘተ... መሠረት ያደረገ ጥላቻን የሚያንጸባርቅ ወይም ጥቃትን የሚያበረታታ ንግግር ማለት እንደመሆኑ፣ የጥላቻ ንግግር በምንም መለኪያ ወይም አመክንዮ ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው፡፡

የጥላቻን ንግግር በሕግ መገደብ በስፋት የተጀመረው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኂላ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በተለይም በዘመነ ናዚ በአገረ ጀርመን የአይሁድ ዘር ባላቸው ሰዎች የታወጀው እልቂት የወቅቱ መንግሥት በይፋ ይነዛው ከነበረው ሰፊ የጥላቻና ለጥቃት የሚያጋልጥ ፕሮፓጋንዳ ጋር ጉድኝት ነበረው፡፡ ስለሆነም፣ በዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት እንዲሁም በብሔራዊ ሕጎች ውስጥ ለችግሩ ትኩረት በመስጠት፣ ሓሳብን በነፃነት መግለጽ ከሚለው መሠረታዊ የሰብዓዊ መብት ጋር የጥላቻ ንግግር በፍጹም እንደማይገናኝ፣ ይልቁንም በሕግ እንዲከለከል፣ እንዲሁም ኃላፊነትና ቅጣትን የሚያስከትል ድርጊት መሆን እንዳለበት ግልጽ አቋም ተወስዶበታል፡፡[29]

የጥላቻ ንግግርን በሕግ የመገደቡ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በአንዳንድ አገሮች ችግሩ ከቁጥጥር ውጭ እስከመሆን የደረሰባቸው ጊዜያት እንደነበሩና አሁንም ሙሉ በሙሉ እንዳልጠፋ የሚያሳዩ ክስተቶች አሉ፡፡ በአሜሪካ የነጭ የበላይነትን በግልጽና በይፋ የሚያውጅና ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት ኃይል እስከመጠቀም የሚደርሰውን ማኅበር (The Ku Klux Clan on White Power) እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ (እ.ኤ.አ) በ1994 በሩዋንዳ የደረሰውን የዘር ጭፍጨፋ ሲያነሳሳ የነበረውና Radio Télévision Libre Des Mille Collines (RTLM) በመባል የሚታወቀው ሬዲዮ ጣቢያ ያሰራጫቸውና የብዙሃኑን ሁቱ ማኅበረሰብ የበላይነት በመስበክ በቁጥር አነስተኛ የሆኑት የቱትሲ ጎሳ አባላት እንዲጠፉ ያሰራጭ የነበረው የጥላቻ መረጃ፣ እንዲሁም በኢጣሊያ የፋሽዝም ደጋፊ ፓርቲ መኖሩና ስደተኞች አገሪቱን ለቀው እንዲወጡ የሚጠይቅ መሆኑ ጥቂት ማሳያዎች ናቸው፡፡[30]

[29] Stephanie Farrior (1996), 'Modeling the Matrix: The Historical and Theoretical Foundations of International Law concerning Hate Speech', *Berkley Journal of International Law* Vol. 14 # 1 ገጽ 25. በተጨማሪም Michael Rosenfield, ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 7 ገጽ 1525 ይመልከቱ

[30] ዝኒ ከማሁ፡፡ በተጨማሪም Jeremy Waldron (2012), *The Harm in Hate Speech*, Harvard University Press, ገጽ 34 ይመልከቱ፡፡

### 5.4 የጥላቻ ንግግር ሕጎች ዓላማና ግብ

በአሁኑ ወቅት 37 (ሠላሳ ሰባት) አገራት የጥላቻ ንግግር ሕግ ያላቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡[31] በእነዚህ አገራት ያሉት ሕጎች ከአጠቃላይ ዓላማና ግባቸው አንፃር በሁለት የሚመደቡ ናቸው፡፡ በመጀመሪያው ጎራ የሚገኙት ሕጎች የጥላቻ ንግግር ዋነኛ መዳረሻ ግቡ መሆን ያለበት ሰብዓዊ ክብርን መጠበቅ (the need to protect human dignity) ነው የሚል አቋም አላቸው፡፡[32] ሕጎቹ በአግባቡ ሥራ ላይ ውለው ከወንጀል ተጠያቂነት በተጨማሪ የፍትሐብሔር ኃላፊነትንም የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የካናዳ፣ ዴንማርክ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመንና ኔዘርላንድ ሕጎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡[33] በሁለተኛው ምድብ የሚገኙት የጥላቻ ንግግር ሕግጋት ደግሞ ከግለሰብ ወይም ከቡድን ባለፈ የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ ከስጋት ለመጠበቅና ለመከላከል (safeguarding public order) ቅድሚያ የሚሰጡ ናቸው፡፡ የሀገረ እንግሊዝ፣ ሰሜን አየርላንድ፣ እስራኤልና አውስትራሊያ ሕግጋት ከዚህ ምድብ ውስጥ ይካተታሉ፡፡[34]

## 6. ሓሳብን የመግለጽ መብትና የጥላቻ ንግግር ሕግ በኢትዮጵያ

### 6.1 ሕገመንግሥታዊ ዳራ

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሕገ መንግሥት ከታወጀበት ከ1923 በፊትም ሆነ በኋላ ሓሳብን በነፃነት መግለጽ ብዙም ያልተለመደ ነበር፡፡ በተለይም ኢትዮጵያውያን የሌሎች አገራትን ልምድ ገሸሽ ማድረጋቸውና፣ በተለይም ለነጮች የነበራቸው አመለካከት ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ ይችላል፡፡[35] ኢትዮጵያ ረጅም የሕግ ታሪክ ያላት አገር ብትሆንም፣ የተጻፈ ሕገ መንግሥት የተደነገገው በ1923 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ ሕገ መንግሥት ሰባት ምዕራፎች (55 አንቀጾች) የነበሩት ሲሆን፣ ስለ ሰብዓዊ መብቶች በሚደነግገው 3ኛው ምዕራፍ (ከአንቀጽ 18 እስከ 29) ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትን በተመለከተ የተገለጸ ነገር የለም፡፡ የተሻሻለው የ1948 ሕገ መንግሥት ስምንት ምዕራፎችና 131 አንቀጾች ነበሩት፡፡ ይህ ሕገ መንግሥት ከ1923 ሕገ መንግሥት በተሻለ መልኩ ከአንቀጽ 37-65 ስለ ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች የሚያወሱ 29 አንቀጾች ነበሩት፡፡ ከነዚህም ውስጥ በአንቀጽ 41 ሥር በመላው ንጉሠ ነገሥት ግዛት ውስጥ በሕግ መሠረት የንግግርና የጋዜጣ ነፃነት የተፈቀደ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ግን  የሌሎችን ሰዎች ነፃነትና መብትን ለማክበርና

---

[31] Radio Interview hosted by Mellisa Block on *Comparing Hate Speech laws in the US and Abroad* with Charles Asher Small-Founder of the Yale Initiative for the interdisciplinary study of Anti-Semtism (March 3, 2011), accessed on 14th August 2021). ይመልከቱ፡፡ በተጨማሪም Chara Bakalis and Ara Ghazaryan (2020), *Comparative Study on Hate speech and Armenian Legislations* (A Research document funded by European Union and Council of Europe of the Project Strengthening access to justice through non-judicial redress mechanisms for victims of discrimination, hate crime and hate speech in Eastern partnership countries) ይመልከቱ፡፡

[32] Jeannine Bell (2009), 'Restraining the Heartless: Racsist Speech and Minority Rights', *Indiana Law Journal*, Vol. 84 issue 3, p. 968

[33] ዝኒ ከማሁ

[34] ዝኒ ከማሁ

[35] በዚህ ጉዳይ ላይ ዝርዝር መረጃንና ማብራሪያን ለማግኘት Teshale Tibebu (1995), *The Making of Modern Ethiopia (1896-1974)*, The Red Sea Press INC., Lawerenceville NJ, USA, pp. 5-7

የሕዝብ ጸጥታና ደህንነትን ለመጠበቅ ሲባል ሁሉም መብቶች ሊገደቡ እንደሚችሉ በአንቀጽ 65 ሥር ተደንግጓል፡፡

ከንጉሠ ነገሥቱ ከሥልጣን መውረድ በኂላ የ1948 ሕገ መንግሥት ተግባራዊነት ሲያበቃ፣ እስከ 1980 ዓ.ም ድረስ (ለ13 ዓመታት) ኢትዮጵያ አለይፋዊ ሕገ መንግሥት ቆይታ በ1980 ዓ.ም የኢ.ሕ.ዲ.ሪ (ኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክሪያሲያዊ ሪፐብሊክ) ሕገ መንግሥት ታወጀ፡፡ በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥም ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት በአንቀጽ 47 ጥበቃ ያደረገለት ቢሆንም፣ በአንቀጽ 58 ላይ ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትን ጨምሮ ሌሎች ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ሁሉ ገደቦች ያሉባቸው መሆኑ ተደንግጓል፡፡ በ1983 ዓ.ም የተደረገውን የመንግሥትና የሥርዓት ለውጥ ተከትሎ የታወጀው የሽግግር ወቅት ቻርተር በአንቀጽ 1(ሀ) ሥር ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ጥበቃ እንዲያገኝ አድርጓል፡፡

በ1987 ዓ.ም ፀድቆ ሥራ ላይ የዋለው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 29 ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የአመለካከትና ሓሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት እንዳለው በግልጽ ይደነግጋል፣ ከዚህም ባሻገር ከቀደሙት የአገራችን ሕግጋተ መንግሥታት ለየት ባለ መልኩ የዚህን መብት ዓይነቶችና ይዘቶች ዘርዘር ባለ መልክ ለማስቀመጥ ሞክሯል፡፡ በተጓዳኝም፣ ሕገመንግሥቱ የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን መልካም ስም ለመጠበቅ፣ የጦርነት ቅስቀሳዎችን ለመከላከል እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሲባል ገደብ እንደሚደረግበት ያስቀምጣል፡፡

### 6.2 የኢትዮጵያ ሕግ ከሕጋዊነት መርህ አኳያ

ከላይ በክፍል 4 በጽንሰ ሓሳብ ደረጃ ከተቀመጡት መርሆች አኳያ፣ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት የተደነገጉትን ገደቦች ከሦስት ዋና ዋና መርሆዎች አንፃር ማየት ይቻላል::[36] የሕጋዊነት መርህን (principle of legality) በሚመለከት፣ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትም ውስጥ ይህ መርህ እውቅና አግኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት፣ ማንኛውም ገደብ ግልጽ በሆነ መልኩ በሕግ የተገለፀ ሊሆን ይገባል::[37] ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ከሓሳቡ ይዘትና ከሚያስከትለው ውጤት አንፃር እንዲሁም ደግሞ የገደቦቹን ዝርዝር በግለጽ ከማሳይት አኳያ[38] የኢትዮጵያን ሕግ ዝርዝር ሕጎች እንዳሉት እንገነዘባለን፡፡

በ1952 የፍትሐብሔር ሕግ (ከአንቀጽ 2044 እስከ 2049) እንዲሁም በ1996 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 613 መሠረት ስም ማጥፋት የፍትሐብሔርና የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል፡፡ በተጨማሪም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 615 ስድብና ማዋረድ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር መሆኑን ደንግጓል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው አንድ ሰው ሓሳቡን በነፃነት የመግለጽ ወይም የመናገር መብት ያለው ቢሆንም፣ የሌላውን ሰው ክብር ወይም ስብዕና በሚነካ መልኩ ስም ማጥፋትም ሆነ መሳደብ ወይም ማዋረድ አይችልም፡፡

ከነዚህ በሕግ ከተቀመጡ ገደቦች በተጨማሪ፣ የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃዎችን ማሰራጨት ሕግ (አዋጅ ቁ. 1185/2012) ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ገደብ እንዲኖረው ያደረገ አዲስ የሕግ ማዕቀፍ ነው፡፡ ይህን ሕግ ለማውጣት በርካታ ሂደቶች

[36] Girmachew A., Yonas B., and Wondmagegn T. (2013), *Ethiopian Human Rights HandBook*, ABA/USAID Publication, Addis Ababa, Ethiopia, p. 104.

[37] ዝኒ ከማሁ

[38] ዝኒ ከማሁ

መታለፋቸውና ብዙ ክርክሮች መካሄዳቸውን በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተዘጋጀው የረቂቅ አዋጅ ማብራሪያ ያሳያል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1185/2012 ውስጥ እንደጥላቻ ንግግር የማይወሰዱ ተግባራት በልዩ ሁኔታነት በአንቀጽ 6 ውስጥ ተገልፀዋል፡፡ ሆኖም ግን፣ በአዋጅ ቁጥር 1185/2012 እንደ ጥላቻ ንግግር እንዳይወሰዱ በልዩ ሁኔታነት የተቀመጡ ንግግሮች/ድርጊቶች የሕጉን አፈፃፀም እና የታለመለትን ዓላማ በማሳካት ረገድ የሚኖራቸውን እንድምታ በሚመለከት፣ አዋጁን አስመልክቶ በተደረጉ የሐሳብ ልውውጦች ውስጥ ትኩረት የተሰጣቸው አይመስልም፡፡ አዋጁ አሥር ቁጥሮችና ሠላሳ አራት ንዑሳን ቁጥሮች የያዘ ሲሆን፣ ዋነኛ ዓላማውም፡-

- ሰዎች ሐሳባቸውን በነፃነት የመግለጽ መብታቸውን ሲጠቀሙ የሌሎችን መብት እንዲያከብሩና ጥላቻን ወይም መድልዎን የሚያስፋፉ ንግግሮች ከማድረግ እንዲቆጠቡ፣
- መቻቻልን፣ የዜጎች ውይይትና ምክክርን፣ መከባበርንና መግባባትን ማበረታታትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ማጎልበት፣
- የጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃዎችን ስርጭት መበራከት መቆጣጠርና መግታት

መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 3 ይገልፃል፡፡ በመሠረቱ በአዋጁ መግቢያ ላይም ሦስት (ከዚሁ አንቀጽ 3 ጋር) ተመሳሳይ የሆኑ ዓላማዎች የተቀመጡ ሲሆን የአዋጁን መንፈስና ምክንያታዊ ዳራ ለመረዳት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ስለሆነም በፍርድ ቤቶችና በማናቸውም ተቋም የሕግ ትርጉምና ውሳኔ አሰጣጥ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ በአዋጅ ቁጥር 1185/2012 አንቀጽ 2(1) እና 2(2) መሠረት የጥላቻ ንግግር ማለት "በቃል፣ በጽሑፍ፣ በምሥልና ሥዕል፣ በቅርጻ ቅርጽና በሌሎች ተመሳሳይ መንገዶች" በመጠቀም "በአንድ ሰው ወይም በተወሰነ ቡድን ማንነት ላይ ያነጣጠረ፣ ብሔርን፣ ብሔረሰብንና ሕዝብን፣ ኃይማኖትን፤ ዘርን፣ ጾታን ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሠረት በማድረግ ሆን ተብሎ ጥላቻን፣ መድሎን ወይም ጥቃትን የሚያነሳሳ ንግግር ማለት ነው" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ ስለሆነም የጥላቻ ንግግር ተደርጎ የሚወሰድ ንግግርን በብሮድካስት፣ በሕትመት ወይም በማኅበራዊ ሚዲያዎች ወይም በሌላ ተመሳሳይ ዘዴዎች አማካኝነት በጽሑፍ፣ በምስል፣ በድምፅ ወይም በቪዲዮ ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡[39]

### 6.3 የጥላቻ ንግግር የድርጊትና የስርጭት ገጽታዎች ከኢትዮጵያ ሕግ አኳያ

የጥላቻ ንግግር የተከለከለ መሆኑን የሚደነግገው አዋጅ ቁጥር 1185/2012፣ አንቀጽ 4 የጥላቻ ንግግር ማሰራጨትን እንጂ የጥላቻ ንግግር ማድረግን በግልጽ ያልከለከለ ሊመስል ይችላል፡፡ ለምሳሌ ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ወይም በአደባባይ በንግግር መልክ (orally) የጥላቻ ንግግር ማድረግን በተመለከተ በአዋጁ ውስጥ ያለው ክልከላ ግልፅ ባይሆንም፣ አጠቃላይ ከአዋጁ ስያሜ ጀምሮ እስከ መሠረታዊ አናቅጾች የተቀመጠው በሙሉ ክልከላ መሆኑን ግንዛቤ በመውሰድ ማሰራጨትን ብቻ ሳይሆን መናገርንም የሚከለክል ድንጋጌ አድርጎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ያልተነገረ ወይም ያልተባለ ነገር ሊሰራጭ አይችልም፡፡ የጥላቻ ንግግሩን ያሰራጨ ሰው እንዲኖርም በመጀመሪያ ንግግሩን ያደረገ ሰው ሊኖር ይገባል፡፡ በዚህ አዎንታዊ መልክ ካልተተረጎመ በስተቀር የጥላቻ ንግግር

---

[39] የጥላቻ ንግግርን እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አዋጅ ቁጥር 1185/2012፣ አንቀጽ 4

አድራጊውና አሰራጩ የተለያዩ ሰዎች በሚሆኑበት ጊዜ ይህ ክፍተት ይበልጥ ጉልህ ሊሆን ይችላል።

ይህ ከሆነ ደግሞ የጥላቻ ንግግር አሰራጩን በወንጀል ኃላፊ ለማድረግ በቅድሚያ የጥላቻ ንግግር ማድረግንም በግልፅ በመከለከል የወንጀል ኃላፊነት እንደሚያስከትል ማስቀመጥ ያስፈልጋል የሚል ክርክር እንዲነሳ በር ሊከፍት ይችላል። በዚህ ነጥብ ላይ የአዋጁን ረቂቅ ብንመለከት፣ የረቂቁ አንቀጽ 4(1) የጥላቻ ንግግርን ወይም ጥላቻ አዘል መልእክቶችን መናገር፣ መፃፍ እንዲሁም ማሰራጨትን በግልፅ ከልክሎ ነበር። ሆኖም ግን አዋጁ በሚፀድቅበት ጊዜ የጥላቻ ንግግርን መናገር እንደተከለከለ ሳይገለፅ የቀረበት ምክንያት ግልፅ አይደለም። በአዋጁ የሚደረጉ ገደቦች የሕጉን ዓላማ ለማሳካት ተመጣጣኝና በጠባቡ የተበጁ መሆን እንዳለባቸው ከሚገልፀው መመዘኛ አንፃር ሲታይ፣ ምናልባትም ተራ ንግግርን ክልከላ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ እንዳልሆነ ተገምቶ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ በአዎንታዊ የትርጉም መርህ (positive interpretation of laws) መሠረት ድንጋጌው የጥላቻ ንግግር ማሰራጨትን ብቻ ሳይሆን ማድረግንም እንደሚጨምር መገንዘብ ያስፈልጋል።

በአደባባይ (ሕዝብ በተሰበሰበበት) ቦታ የሚደረጉ የጥላቻ ንግግሮችን የሚመለከቱ ድርጊቶች በአዋጁ በግልፅ ባይካተቱም የሚስተናገዱበት አግባብ በጥንቃቄ ሊመረመር ይገባል። በአደባባይ የሚደረጉ የጥላቻ ንግግሮች የሚያስከትሉት ጉዳት ቀላል ባለመሆኑ ከተራ ንግግሮች ጋር በተመሳሳይ መንገድ የሚታዩ አይሆኑም። ምንም እንኳን የአደባባይ ንግግሮች በአንቀጽ 4 ሥር ባለው ክልከላ በግልጽ ባይካተቱም፣ በዚህ ረገድ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት ከላይ የተቀመጠውን የትርጉም መርህ መከተል የግድ አስፈላጊ ነው።

በተጨማሪም በአዋጁ አንቀጽ 2(7) "ማሰራጨት ማለት ንግግርን *በማናቸውም መንገዶች ለብዙ ሰዎች እንዲደርስ ማድረግ* ሲሆን በማኅበራዊ ሚዲያ ላይክ [like] ማድረግና ታግ ማድረግን አያካትትም፣" (አጽንኦት የተጨመረ) በማለት ትርጓሜ ተሰጥቶታል። ስለሆነም ሌሎች ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በአደባባይ የሚነገሩ የጥላቻ ንግግሮች የጥላቻ ንግግር ማሰራጨትን በከለከለው አንቀጽ 4 ሥር አይካተቱም ለማለት አይቻልም። በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2(4) አንፃር ሲታይም፣ አጠራጣሪ የሆኑ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችን በሕጉ አጠቃላይ መንፈስና ዓላማ መሠረት መተርጎም ተገቢነት ያለው ነው።

### 6.4 በጥላቻ ንግግር አተረጓጎም ረገድ በአዋጅ ቁጥር 1185/2012 የሚታይ ክፍተት

ስለጥላቻ ንግግር በአዋጅ ቁጥር 1185/2012 ውስጥ የተሰጠው ትርጓሜ ሰፊና ለግላዊ አረዳድ (subjectivity) ተጋላጭ የሆኑ ቃላትን የያዘ መሆኑ አዋጁ በረቂቅነት ደረጃ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሲቀርብ የነበረ ስጋት ነው።[40] በሌላ በኩል የጥላቻ ንግግርን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በመብቶች ላይ የሚጣሉ ገደቦች "በዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ

---

[40] Girmachew Alemu, *Narrow Hate Speech Law Will Not Broaden Minds*,(January 24, 2020), available at https://www.ethiopia-insight.com/2020/01/24/narrow-hate-speech-law-will-not-broaden-minds/ ፤ Yohannes Eneyew Ayalew, *Muting Sectarianism or Muzzling Speech*?, (2020), available at፡ https://www.ethiopia-insight.com/2020/01/31/muting-sectarianism-or-muzzling-speech/ ፤ የጥላቻ ንግግርና የሃሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ አጭር ማብራሪያ፣ ገፅ 2

ውስጥ ተቀባይነት ያለውን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ፣ ተመጣጣኝና በጠባቡ የተበጁ መሆን እንዳለባቸው…" በአዋጁ መግቢያ ላይ ተገልጧል፡፡ ስለሆነም የአዋጁ አንቀጽ 6 በአዋጁ የሚካተቱ ክልከላዎችን ተመጣጣኝ የማድረግ ዓላማ አለው ማለት ይቻላል፡፡ አዋጁ የጥላቻ ንግግር ለሚለው ትርጉም ሲሰጥ ጥላቻ (hate or hatred) ለሚለው ጽንሰ ሐሳብ ትርጉም አልሰጠም፡፡ አዋጁ "…ጥላቻን፣ መድሎን ወይም ጥቃትን የሚያነሳሳ ንግግር" በማለት የጥላቻ ንግግርን በተረጎመበት ድንጋጌ ጥላቻ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ወይም ምን ምን ነገሮች ሲሟሉ እንደሚገባ የሚገልጽ ድንጋጌ፣ መስፈርት ወይም መለኪያ አላካተተም፡፡

ታዋቂው የሕግ መዝገበ ቃላት ጥላቻ ለሚለው ጽንሰ ሐሳብ ትርጉም የሚሰጠው የጥላቻ ወንጀል (hate crime) ወይም የጥላቻ ንግግር ከሚሉት ነጥቦች ጋር በማያያዝ ነው ፡፡[41] በመደበኛው የእንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት ደግሞ ጥላቻ (hate or hatred) ለሚለው ቃል የተሰጠው ትርጉም የሚከተለው ነው፡-

"Hate means to dislike somebody or something intensly or to find something unpleasant or the emotion of intense dislike".[42] (ጥላቻ ማለት ስለ አንድ ነገር ወይም ሰው የሚሰማን መጥፎ ወይም ጥሩ ያልሆነ ስሜት ወይም አሉታዊ ስሜት ማለት ነው፡፡)

ሐሳብን በነፃነት የመግለጽና የእኩልነት መብትን በተመለከተ፣ የካምደን መርሆዎች (The Camden Principles on Freedom of Expression and Equality)፣ መርህ ቁጥር 12 ጥላቻን እንደሚከተለው ተርጉሞታል፡-

"The terms 'hatred' and 'hostility' refer to intense and irrational emotions of opprobrium, enmity and detestation towards the target group". (ጥላቻ ማለት ስሜታዊ በሆነና ኢምክንያታዊ በሆነ መልኩ በአንድ ተለይቶ በሚታወቅ ቡድን ላይ በሚያዋርድና የጠላትነትን ስሜት በሚያንጸባርቅ እንዲሁም በሚያስጸይፍ መልኩ የሚሰነዘር አገላለጽ/አጠራር ወይም ንግግር ማለት ነው፡፡)[43]

ከእነዚህ ትርጉሞች መረዳት እንደሚቻለው፣ ጥላቻ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ስለአንድ ነገር ያለንን በጎ (ጥሩ) ያልሆነ ወይም መጥፎ ስሜት የሚመለከት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የጥላቻ ስሜት በቃል ወይም በድርጊት እስካልተገለጸ ድረስ ተጠያቂ ሊያደርግ አይችልም፡፡ በዚህ ጽሁፍ አቅራቢዎች እምነት ግን ቢያንስ ሕጉ ከላይ የተጠቀሱትን የካምደን መርሆዎችን በመጠቀም መነሻ የሆነ ትርጉም ቢያስቀምጥ (አስቸጋሪና ለግላዊ አረዳድ /subjectivity/ የተጋለጠ ቢሆንም እንኳ) የተሻለና አዋጁንም የበለጠ ምሉዕ ማድረግ ይቻል ነበር፡፡

ሌላው ከትርጉም ጋር ተያይዞ የሚነሳው ነጥብ በአዋጁ አንቀጽ 2(2) ላይ የተገለጸው የማነሳሳት ጉዳይ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው፣ የጥላቻ ንግግር "በቃል፣ በጽሑፍ፣

---

[41] B.A. Garner (Ed.), 2004, *Black's Law Dictionary*, 8th ed., pp. 1122 and 4381

[42] J. Crowther (Ed.), 1995, *Oxford Advanced Learner's Dictionary of Current English*, 5th Ed., Oxford University Press, p. 546.

[43] *The Camden Principles on Freedom of Expression and Equality*, Principle no. 12 (April 2009), Article XIX Global Campaign For Free Expression, p. 10. ይመልከቱ፡፡ በተጨማሪም Yohannes E. Ayalew, (2020), 'Defining Hate Speech under the Hate Speech Suppression Proclamation in Ethiopia, A Sisyphean Exercise?', *Ethiopian Human Rights Law Series*, Vol. 12, p. 3 ይመልከቱ፡፡

በምሥልና ሥዕል፣ በቅርጸ ቅርጽና በሌሎች ተመሳሳይ መንገዶች በመጠቀም በአንድ ሰው ወይም በተወሰነ ቡድን ማንነት ላይ ያነጣጠረ፣ ብሔርን፣ ብሔረሰብንና ሕዝብን፣ ኃይማኖትን፤ ዘርን፣ ጾታን ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሠረት በማድረግ ሆን ተብሎ ጥላቻን፣ መድሎን ወይም ጥቃትን የሚያነሳሳ ንግግር" ነው። ይህን የአዋጁን ድንጋጌ ከአንቀጽ 4 ጋር አስተሳስረን ስናየው በአንቀጽ 2(2) የተቀመጠውን የጥላቻ ንግግር የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅሞ ማሰራጨት የተከለከለ መሆኑን እንረዳለን። የዚህን የጥላቻ ንግግር ወንጀል ለማቋቋም አንድ ሰው የጥላቻ ንግግር መናገሩ ወይም ማሰራጨቱ ብቻ ሳይሆን በዚህ በተሰራጨው ንግግር የተነሳሳ አካል መኖሩና ይህ የተነሳሳ አካል ሌላ አካል ላይ ጉዳት ወይም ጥቃት ማድረስ መቻል አለበት ማለት ነው ብሎ መከራከር ይቻላል።

ነገር ግን የአዋጁን አንቀጽ 7(1) እና (2) ስንመለከት፣ የጥላቻ ንግግሩ አንቀጽ 4ን በመተላለፍ ተሰራጭቶ ነገር ግን በዚሁ ንግግር ምክንያት የተነሳሳ አካል ከሌለና የደረሰ ጥቃት ከሌለ የሚጣለው ቅጣት፣ በንግግሩ በመነሳሳት ሌሎች አካላት ላይ ጥቃት ከደረሰ ከሚጣለው ቅጣት የተለየ ከመሆኑ አኳያ፣ ማነሳሳት የሚለውን ነጥብ በጥንቃቄ መመልከት እንዳለብን እንገነዘባለን። ምንም እንኳን አከራካሪ ቢሆንም፣ ለምሳሌ በአዋጁ አንቀጽ 6(1)(መ) ላይ እንደ ጥላቻ ንግግር ከማይቆጠሩት ልዩ ሁኔታዎች መካከል አንዱ የሆነው ኃይማኖታዊ አስተምህሮ ነው። ለዚህ ድንጋጌ አላግባብ ሰፊ ትርጉም በመስጠት፣ አንድ ሰው የራሱን ኃይማኖታዊ እምነት ሲያስተምር ከሌሎች የእምነት ተቋማት አስተምህሮ ጋር በማነጻጸር የራሱ አቋም ምን ያህል ትክክል እንደሆነና ሌሎቹ እንደተሳሳቱ ቢያስተምርና ቢተች፣ ጥላቻ ሊከሰት ይችላል። በዚህ ምክንያት ምዕመናኑ ወይም ታዳሚዎቹ በሌሎች የእምነት ተቋማት ላይ ጥላቻ ቢያድርባቸው እና አላግባብ ቢነሳሱ፣ ተጠያቂነቱ እንዴት ይታያል? ወይም የማነሳሳት መነሻው ወይም ዝቅተኛ መለኪያው/መስፈርቱ (threshold) ምንድነው የሚለው ምላሽ ማግኘት ይኖርበታል።

ከትርጉም ጋር በተያያዘ የሚነሳው ሌላው ነጥብ የጥላቻ ንግግር የሚያነጣጥርባቸው አካላት እነማናቸው የሚለው ጉዳይ ነው። አዋጁ የጥላቻ ንግግር ያነጣጥርባቸዋል ብሎ የወሰናቸው አካላት ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ፣ ኃይማኖት፣ ዘር፣ ጾታ ወይም አካል ጉዳተኝነት ናቸው። በተመሳሳይ መልኩ የፌስቡክ (ማኅበራዊ ድረ-ገጽ) የማኅበረሰብ ስታንዳርድ ስለጥላቻ ንግግር ትርጉም ሲሰጥ ጥበቃ የሚደረግላቸው ቡድኖችን ዘርዝሯል። በተጨማሪም እ.ኤ.አ. በ1948 የወጣው የሰው ዘር ማጥፋት ወንጀልን ለመከላከልና ለመቅጣት የተደረገው ስምምነት (Convention to prevent and punish the crime of Genocide of 1948) አንቀጽ 2 ላይ ዘርን ማጥፋት ማለት ሆን ብሎ በከፊልም ሆነ በሙሉ የአንድን ብሔር፣ ጎሳ፣ዘር ወይም ኃይማኖት ወገን ማጥፋት ማለት ነው በማለት ትርጉም ይሰጠዋል።

ምንም እንኳ በርካታ የዓለምዓቀፍ ወንጀል ሕግ (International Criminal Law) ተመራማሪዎች ባይቀበሉትምና ዘር ማጥፋት የሚለውን ጽንሰ ሓሳብ አግባብ ባልሆነ መንገድ ይለጥጣል በማለት ቢተቹትም፣ በ1996 የወጣው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 269 መሠረት "ማንም ሰው በሰላምም ሆነ በጦርነት ጊዜ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጎሳ፣ በዘር፣ በዜግነት፣ በቀለም፣ በኃይማኖት ወይም በፖለቲካ አንድ የሆንን ቡድን በመላ ወይም በከፊል ለማጥፋት በማሰብ የጥፋቱን ድርጊት በማደራጀት፣ ትዕዛዝ በመስጠት ወይም ድርጊቱን" መፈጸም እነደዘር ማጥፋት የሚቆጠር በመሆኑ "የፖለቲካ ቡድን" ጭምር እንዲካተት ተደርጓል። "በፖለቲካ አንድ የሆነን ቡድን" የሚለው ሐረግ የሚመለከተው የፖለቲካ ማኅበረሰብን (political entity) ነው ወይስ ፖለቲካ ፓርቲን ይጨምራል የሚለው ክርክር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሁለተኛውን አተረጓጎም ከተከተልን

የአንድ የፖለቲካ ሓሳብ ወይም አመለካከት አራማጅ በሆነ ቡድን ላይ የሚደረግ ቡድኑን የማጥፋት ሥራ በወንጀል የሚያስጠይቅ እንደሆነ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል። የጥላቻ ንግግርን ለመከልከል የወጣው አዋጅ ቁ. 1185/2012 አንቀጽ 2ም በተመሳሳይ መልኩ የጥላቻ ንግግር ኢላማ ተብለው ከተዘረዘሩት አካላት መካከል የአንድ የፖለቲካ ሓሳብ ወይም አመለካከት አራማጅ የሆኑ ቡድኖችንም መጨመር ነበረበት ማለት ነው።

በዚህ መልኩ ይህን ሕግ ተጠቅሞና በፖለቲካ አመለካከቴ ወይም ሓሳቤ ምክንያት ጉዳት ወይም ጥቃት ደርሶብኛል በሚል ለፍርድ ቤት ክስ የሚያቀርብ አካል ቢመጣ በምን መልኩ ሊስተናገድና ፍትሕ ሊያገኝ እንደሚችል ግልጽ አይደለም የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል። እንደጸሓፊዎቹ እምነት፣ የአዋጁ አንቀጽ 2 ማለትም የጥላቻ ንግግር ትርጓሜን የያዘው ድንጋጌ ጠቅለል ባለ መልኩ የተቀመጠ (catch-all phrase) እንደመሆኑ፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም ሓሳብ ምክንያት ጥቃት ማድረስንም የሚጨመር መሆኑ ግንዛቤ ተወስዶ በዚህ መልኩ ሊተረጎምና የውሳኔ መሠረት ሊደረግ ይገባል። በድንጋጌው የአማርኛና የእንግሊዘኛ ትርጉም መካከል ያለው አለመጣጣምም ቢሆን፣ የአማርኛው ቅጂ ገዥነት ያለው መሆኑ ስለሚታወቅ ያን ያህል አፈጻጸም ላይ ችግር ያስከትላል ተብሎ አይታሰብም።

እዚህ ላይ የሚነሳው ሌላ ነጥብ የጥላቻ ንግግር በ1996 የወንጀል ሕግ፣ በተለይም በአንቀጽ 613 ላይ የተገለፀው ስም ማጥፋትና የሓሰት ሐሜት (defamation and calumny) እንዲሁም በአንቀጽ 615 የተቀመጠው ስድብና ማዋረድ (insulting and outrage behavior) ወንጀሎች ጋር ያለው ተዛምዶና ልዩነት ነው። በተጠቀሱት የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች የተጠቀሱት ድርጊቶች በግለሰብ ሰብዓዊ ክብር ወይም መልካም ስም ላይ የተቃጡና ከዚያ ያለፈ ውጤት ይኖራቸዋል ተብለው የማይገመቱ የወንጀል ድርጊቶች ሲሆኑ፣ የጥላቻ ንግግር ግን ከግለሰብ አልፎ ግለሰቡ የሚወክለውን ወይም አባል/ተወላጅ የሆነበትን ብሔር ወይም ኃይማኖት ወይም ጾታ ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሠረት በማድረግ በሌሎች ዘንድ እንዲጠላ ወይም እንዲገለል ወይም እንዲጠቃ/ጥቃት እንዲደርስበት የሚያነሳሳ ድርጊት ነው። ከግለሰብ ወይም ከቡድን ባለፈም የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ ከስጋት መጠበቅና መከላከል ነው (safeguarding public order) የሚል አቋም ካላቸው አገራት ሕግጋት ጋር የሚመደብ ነው ማለት ይቻላል።

### 6.5 የጥላቻ ንግግርና ሓሰተኛ መረጃዎች ሕግ ጥሰት ተፈጻሚነት ወሰን

በአዋጁ ክፍል ሁለት የተከለከሉ ተግባራት በሚለው ርዕስ ሥር የጥላቻ ንግግርም ሆነ ሓሰተኛ መረጃዎችን ማሰራጨት፣ እንዲሁም በልዩ ሁኔታ የሚታዩ ድርጊቶች ተዘርዝረው ተቀምጠዋል። በአንቀጽ 4 የጥላቻ ንግግርን በብሮድካስት፣ በሕትመት ወይም በማኅበራዊ ሚዲያ በጽሁፍ፣ በምስል፣ በድምጽ ወይም በቪድዮ ማሰራጨት የተከለከለ ሲሆን በአንቀጽ 5 የሐሰት መረጃን በብሮድካስት፣ በሕትመት ወይም በማኅበራዊ ሚድያ በጽሁፍ፣ በምስል፣ በድምጽ ወይም በቪድዮ ማሰራጨት የተከለከለ መሆኑ ተደንግጓል። በእርግጥ አዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን የሚገልጽ ድንጋጌ ባይኖረውም ከነዚህ ሁለት አንቀጾች (አንቀጽ 4 እና አንቀጽ 5) መረዳት እንደሚቻለው አዋጁ ይህንን ሕግ ተላልፈው ጥፋት በሚፈጽሙ የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት በተሰጣቸው ማናቸውም ሰዎች ላይ ተፈፃሚነት አለው። ይህም ከወንጀል ድርጊቱ አደገኛነት ባህርይና ከሚያስከትለውም ጥፋት ከባድነት አንፃር ተገቢ ነው።

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ሌላው ነጥብ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 29 ድንጋጌዎች ውስጥ መጣረስ ያለና ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትን በአግባቡ ለመጠቀም ለማስቻል ታስበው ገድብ በሚያስቀምጡ ሕግጋት ላይ የአፈጻጸም ችግር ሊያስከትል ይችላል የሚል ስጋት በአንዳንድ ወገኖች መኖሩ ነው። በመሠረቱ የሕገ

መንግሥቱ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አመዳደብ በራሱ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ በዚህ መልኩ መብቶችን መከፋፈል ተገቢ አለመሆኑና በዓለምዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ ድጋፍ የሌለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በተለይም በአንቀጽ 29 ሥር በተቀመጡት ንዑሳን ድንጋጌዎች/ቁጥሮች (በንዑስ ቁ. 1-6) መሠረት ማንኛውም ሰው ሓሳቡን በነፃነት የመግለጽ መብት እንዳለውና ይህንንም መብቱን ያለማንም ጣልቃ ገብነት መጠቀም እንደሚችል ነገር ግን በሕግ ገደቦች ሊጣሉ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን፣ የአንቀጹ የመጨረሻ ንዑስ ቁጥር (አንቀጽ 29 ንዑስ ቁጥር 7) ሕጉ ከንዑስ ቁጥር 1 እስከ 6 የመጣበትን አካሄድ የሳተ በሚያስመስለው አኳኋን በመብቱ አጠቃቀም የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦችን (ለምሳሌ ይኸው የጥላቻ ንግግር ሕግ) ጥሶ ከተገኘ ተጠያቂው *ማንኛውም ዜጋ* እንደሚሆን ስለሚደነግግ ኢትዮጵያዊ ያልሆነን ጥፋተኛ የሚመለከት ጥያቄ ያስነሳል፡፡

በእርግጥም በተራ ንባብ ከተወሰደ ይህ የቃላት መጣረስ ወይም ቴክኒካዊ ስህተት (drafting error) ሊመስል ይችላል፡፡ ምክንያቱም *የኢትዮጵያ ዜጋ* የሆነ ሰው የሚኖሩት መብቶችና የሚጣሉበት ግዴታዎች የኢትዮጵያ ዜጋ ካልሆነ ሰው ጋር በእጅጉ የተለያየ ስለሆነና በዚህም ምክንያት ይህ የጥላቻ ንግግር ወንጀል ድርጊት የኢትዮጵያ ዜጋ ባልሆነ ሰው ከተፈጸመ ሕጉ ተፈጻሚነት አይኖረውም የሚል ትርጉም ሊሰጥ አይገባም፡፡ ይህ የአተረጓጎም ጥንቃቄ ካልተደረገ በቀር የአዋጁ አንቀጽ 4 እና 5 ድንጋጌዎች ትርጉም አልባ ይሆናሉ፡፡ በተቃራኒው የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 29(7) ድንጋጌ ወደጎን በማድረግ የአዋጁ አንቀጽ 4 እና 5 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሁኑ ቢባል ደግሞ፣ የሕገ መንግሥቱና የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎችን የበላይነትን ጥያቄ ውስጥ የሚከት ይሆናል፡፡ (ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1) እና አንቀጽ 13(2) ይመለከቷል፡፡)

ስለሆነም፣ ይህ የሕገ መንግሥት ድንጋጌ አንድም ይፋዊ ባልሆነ የሕገመንግሥት ማሻሻያ (informal constitutional amendment) ማለትም በሕገ መንግሥት ትርጉም ወይም በይፋዊ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ (formal constitutional amendment) ሥርዓት መሠረት መስተካከል ይኖርበታል ተብሎ ሊታሰብ ይችላል፡፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 29(7) "ማንኛውም ዜጋ" የሚለው ሐረግ የኢትዮጵያ ዜጋ ወይም ኢትዮጵያዊ ዜጋን ብቻ ሊመለከት እንደማይችል ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም የሕገ መንግሥቱ አርቃቂዎች ሓሳብ ይህ ቢሆን ኖሮ እንደሌሎቹ ድንጋጌዎች፣ ለምሳሌ በአንቀጽ 38(1) የመምረጥና የመመረጥ መብትን በሚመለከት እንዲሁም በአንቀጽ 40 (የንብረት መብትን በተመለከተ) በተደነገገው አኳኋን፣ "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ"፣ "ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ" ወዘተ. የሚሉ አገላለፆችን በተጠቀሙ ነበር፡፡ ስለኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባህል መብቶች በሚደነግገው በአንቀጽ 41 አርቃቂዎቹ የተጠቀሙትም አገላለፅ "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ" የሚል እንደመሆኑ፣ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 29(7) ኢትዮጵያዊ ዜጋን ብቻ የሚመለከት ድንጋጌ ቢሆን ኖሮ ተመሳሳይ አገላለፅ ይከተሉ ነበር፡፡

### 6.6 እንደ ጥላቻ ንግግር የማይቆጠሩ ልዩ ሁኔታዎች

በአዋጁ አንቀጽ 6 የጥላቻ ንግግር የተከለከለ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በልዩ ሁኔታ የሚታዩ ነጥቦችን የሚዘረዝር ሲሆን፣ አንድ ንግግር እንደ ጥላቻ ንግግር እንዳይወሰድ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል አንዱ ንግግሩ በንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የትምህርታዊ ወይም ሣይንሳዊ ምርምር አካል ከሆነ ነው፡፡"[44] ምንም እንኳን የአዋጁ አጭር ማብራሪያ ይህ

[44] አዋጅ ቁ. 1185/2012፣ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 39፣ አንቀጽ 6(1)(ሀ)

ልዩ ሁኔታ ሊያሳካ የፈለገውን ዓላማ በተመለከተ የሚናገረው ነገር ባይኖርም፣ ድንጋጌው የጥላቻ ንግግርን ለመከላለከል የወጣው ሕግ ትምህርታዊ ወይም ሣይንሳዊ ምርምር ማድረግን በተመለከተ እና የምርምር ውጤት በመግለጽ ላይ ጫና እንዳይፈጠር ለመከላከል የታለመ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ለምሳሌ፣ የዘር ማጥፋትን የሚክድ እና የሚያሳንስ ተግባር መፈፀምን በከለከለው የሩዋንዳ ሕግ ምክንያት በዘር ማጥፋት ላይ የሚጻፉ መደበኛ ትምህርታዊ ጽሑፎች እና ውይይቶች እንደ ወንጀል እየተቆጠሩ ክስ የተመሠረተባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡[45] ሆኖም ግን በተባበሩት መንግሥታት ሰብዓዊ መብቶች ኮሚቴ አጠቃላይ ትንታኔ ቁ. 34 (General Comment no. 34) መሠረት እንዲህ ዓይነት የዘር ማጥፋት ድርጊቶችንና እውነታዎችን መካድ፣ ለምሳሌ የሩዋንዳውንና በዘመነ ናዚ የተፈፀመውን የዘር ማጥፋት ታሪክና እውነታን መካድ ወይም አልተፈጸመም ብሎ መከራከር እንደጥላቻ ንግግር ተወስዶ በገደብነት ሊቀመጥ አይገባም፣ ወይም ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትን አላግባብ ተጠቅመሃል ተብሎ ግለሰቡ ሊጠየቅ አይገባም በማለት አቋም መያዙ ይታወቃል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 6(1)(ሀ) የትምህርታዊ ወይም ሣይንሳዊ ምርምር አካል የሆኑ ንግግሮችን በልዩ ሁኔታነት ያስቀመጠው ይህን ዓይነት ያልተፈለጉ እና ሕጉ ሊያሳካ ከፈለገው ዓላማ ጋር አብረው የማይሄዱ የወንጀል ክሶችን ለማስቀረት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

ሌላው በአዋጁ እንደ ጥላቻ ንግግር ተደርጎ በልዩ ሁኔታነት የተቀመጠው ንግግሩ "የዜና ዘገባ፣ ትንታኔ ወይም ፖለቲካ ትችት አካል እንደሆነ ነው፡፡"[46] አንድ ንግግር የኪነጥበብ፣ ትወና ወይም መሰል የሥነጥበብ ውጤት ከሆነ እንደ ጥላቻ ንግግር አይወሰድም፡፡[47] እንዲህ ዓይነት ሥራዎች እንደ ጥላቻ ንግግር የማይወሰዱት ሥራዎቹ ጥላቻን፣ መድሎን ወይም ጥቃትን ከማነሳሳት ይልቅ ሰውን ማዝናናት ላይ ያተኮሩ ናቸው በሚል እሳቤ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለይም የፖለቲካ ትችት ወይም ንግግር በዋነኛነት ሐሳብን በነፃነት መግለጽ መብት ከሚንጸባረቅባቸው መንገዶች አንዱ ስለሆነና ተጨማሪ የሕግ ከለላ ስላለው ጭምር ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ሌላኛው በአዋጁ ውስጥ በተካተቱት ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ እንደ ጥላቻ ንግግር እንዳይወሰድ የተገለፀው የኃይማኖታዊ አስተምህሮት አካል የሆነ ንግግር ነው፡፡[48] ይህም የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አዋጁ የሚያስቀምጣቸውን ክልከላዎች አስፈላጊ እና ተመጣጣኝ የማድረግ አጠቃላይ መርህ አንድ አካል ነው፡፡ በዜጎች የኃይማኖት እና እምነት ነፃነት ላይ የአዋጁ ክልከላ እና አተገባበር ሊኖረው የሚችለውን አሉታዊ ውጤት ለማስወገድ የተደረገ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተገለፁት የአንቀጽ 6 ንዑሳን አንቀጾች መካከል በአንዱ ውስጥ የሚካተቱ ንግግሮች በአዋጁ ክልከላ ያልተደረገባቸው ስለሆኑ ድርጊቶቹን ተከትሎ አዋጁን መሠረት በማድረግ ሊመጣ የሚችል የወንጀል ኃላፊነት አይኖርም፡፡ ነገር ግን በንዑሳን አንቀጾች ውስጥ የተካተቱት ሐሳቦች ጥቅልና ግልፅነት የጎደላቸው በመሆናቸው አዋጁን በመተግበር ሂደት ችግር ማስከተላቸው አይቀርም፡፡

---

[45] Law no. 59/2018 of 22nd August 2018 on the crime of Genocide ideology and related crimes Art. 4. (Kigali, Rwanda) ይመልከቱ፡፡ በተጨማሪም *Henry Maina*, ግርጌ ቁጥር 20 ላይ ይመልከቱ፡፡

[46] አዋጅ ቁ. 1185/2012፣ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 39፣ አንቀጽ 6(1)(ለ)

[47] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 6(1)(ሐ)

[48] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 6(1)(መ)

# 7. ስለጥላቻ ንግግር ልዩ ሁኔታዎች ትኩረት የሚሹ አንዳንድ ነጥቦች

አንድ ንግግር እንደ ጥላቻ ንግግር እንዳይወሰድ የሚያደርጉ ምክንያቶችን አስመልክቶ በአዋጁ ውስጥ በተዘረዘሩት ልዩ ሁኔታዎች ላይ የሚነሳው የመጀመሪያው ጥያቄ፣ ንግግሩ በልዩ ሁኔታነት በተቀመጡት ተግባራት መልክ መደረጉ ብቻውን እንደ ጥላቻ ንግግር እንዳይወሰድ ሊያደርግ ስለመቻል/አለመቻሉ ነው፡፡ ይህ ጥያቄ የሚነሳበት አንዱ ምክንያት ምንም እንኳን ንግግሮቹ በአንቀጽ 6 ሥር ከተዘረዘሩት መካከል የሚገኙ ቢሆንም፣ አዋጁ ጥበቃ ባደረገላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ የተፈፀሙ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ፡፡

## 7.1 የሥነ-ጥብበ ውጤት መስለው የሚቀርቡ የጥላቻ ንግግሮች

የሩዋንዳውን የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲመለከት በነበረው ዓለምአቀፍ ፍርድ ቤት፣ የዘር ማጥፋትን የሚያበረታቱ ሙዚቃዎችን በመሥራት ተሳታፊነት የነበራቸው ሰዎች ጭምር ተከሰው ነበር፡፡[49] እነዚህ ሥራዎች ምንም እንኳን በውስጣቸው የሥነጥበብ ውጤት የሚመስሉ እንደ ተረት፣ ተምሳሌታዊ ንግግርና የመሳሰሉትን አካተው ቢቀርቡም፣ በይዘታቸው ለአድማጩ ማኅበረሰብ ሊያስተላልፉት የሚፈልጉት የጥላቻ እና ለጥቃት ማነሳሳት መልእክት ግልፅ ሆኖ ሊገኝ ይችላል፡፡[50] ይህ በተለይ ባህላዊ ዘፈኖች እና ሌሎች ባህል-ነክ የኪነጥበብ ውጤቶች ላይ ሊከሰት ስለሚችል እነዚህ ዓይነት ሥራዎች የሚያስተላልፉትን መልዕክት እና የተሠሩበትን ዓላማ ለማወቅ የማኅበረሰቡን ባህል፣ ቋንቋ ፣ወግ ወዘተ ማወቅ እና ሥራዎችንም ከዚያው አንፃር መመርመር ተገቢ ነው፡፡[51] ይህን በማድረግ ሂደትም ላይ ላዩን ሲታዩ የሥነ-ጥበብ ውጤት የሚመስሉ ሥራዎች ከውስጣቸው ግን የጥላቻ ንግግርን ያዘሉ እና በአንድ የማኅበረሰብ ክፍል ላይ ጥላቻን፣ መድሎን እንዲሁም ጥቃትን የሚያነሳሱ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ፡፡

ይህን መሰል ጉዳዮች በኢትዮጵያም ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም ጥላቻ፣ መድሎ ወይም ጥቃትን የሚያነሳሳ የጥላቻ ንግግር በራሱ (*per se*) ንግግሩን ተከትሎ የደረሰ ጉዳት ባይኖርም በአዋጅ ቁጥር 1185/2012 የተከለከለ ነው፡፡ ስለሆነም እነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ከተከሰቱ በልዩ ሁኔታ ድንጋጌዎች መሠረት ተከሳሾች ነፃ ይሆናሉ ወይስ በአዋጁ የጥላቻ ንግግርን ማሰራጨትን በከለከለው ድንጋጌ መሠረት ተጠያቂ ይደረጋሉ? ለሚለው ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይገባል፡፡

## 7.2 ትምህርታዊ ወይም ሣይንሳዊ ምርምር መስለው የሚቀርቡ የጥላቻ ንግግሮች

ጥቃትን፣ መድሎን ወይም ጥላቻን የማነሳሳት ዓላማ ያላቸው ሰዎች መልዕክቶቻቸውን ትምህርታዊ ምርምር አስመስለው የሚያሰራጩበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል፡፡[52] ይህ

---

[49] *Comparative Hate Speech Law: Annexture*, Research prepared for the Legal Resources Centre, South Africa፣ (March 2012) ፣ Oxford Pro Bono Publico http://www.law.ox.ac.uk/opbp p. 46 ይመልከቱ፡፡ በተጨማሪም *The Prosecutor vs. Ferdinand Nahimana, Jean-Bosco Barayagwiza and Hassan Ngeze* (Appeal Judgment) ICTR-99-52-A, International Criminal Tribunal for Rwanda (ICTR), 28 november 2007 ይመልከቱ

[50] Comparative Hate Speech Law፣ ዝኒ ከማሁ፣ p. 31 & 47

[51] ዝኒ ከማሁ

[52] ዝኒ ከማሁ

ተግባር፣ ሊመጣ ከሚችል የሕግ ተጠያቂነት ለማምለጥ እንዲቻል ሽፋን ለማግኘት በማሰብ የሚሠራ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ረገድ ግምት ውስጥ መግባት ካለባቸው ነጥቦች ውስጥ አንደኛው የጥላቻ ንግግርን በመበየን ሂደት ንግግሩ ብቻ ሳይሆን የንግግር አድራጊው የሓሳብ ክፍል (intent) ትልቅ ሥፍራ የሚይዝ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ሰው በሕግ አግባብ እንደ ጥላቻ ንግግር የሚወሰዱ ንግግሮችን ቢፈፅም፣ በጥላቻ ንግግር ይከሰስ ዘንድ ተግባራቱን የፈፀመው ሆን ብሎ ጥላቻን፣ መድሎን ወይም ጥቃትን ለማነሳሳት በማሰብ ሊሆን ይገባል፡፡[53]

ይህንን የሓሳብ ክፍል (intent) ወደ ልዩ ሁኔታ ድንጋጌዎች ስናመጣው፣ አንድ ንግግር እንደ ልዩ ሁኔታ ተወስዶ የማያስቀጣ ይሆን ዘንድ የንግግሩ ዓላማ በልዩ ሁኔታ ድንጋጌው ውስጥ የተመለከቱትን ተግባራት ለማከናወን ብቻ ያለመ መሆን አለበት፡፡ ይህም ማለት፣ ምንም እንኳን ንግግሩ በንዑስ አንቀጾቹ ሥር የተዘረዘሩት ተግባራት አካል ቢሆንም የንግግሩ ዓላማ ግን ሆን ተብሎ ጥላቻን፣ መድሎን ወይም ጥቃትን ማነሳሳት መሆኑ ከተረጋገጠ በልዩ ሁኔታነት መታየቱን በማስቀረት በወንጀል ተጠያቂ ያደርጋል ማለት ነው፡፡ በአዋጁ ማብራሪያ እንደተገለፀው፣ "*ከእነዚህ ከተገለፁት መንገዶች ለአንደኛው ዓላማ የሚደረግ ንግግር እንደ የጥላቻ ንግግር …ተወስዶ የሚከለከልና የሚያስቀጣ አይሆንም*"፡፡[54] (አጽንኦት የተጨመረ)፡፡ ስለዚህ የሓሳብ ክፍልን (intent) ለመረዳት፣ የክስ መነሻ የሆነውን ንግግር ብቻ በተናጠል በመውሰድ ሳንወሰን፣ ሙሉ ንግግሩን ማየት ያሻል ማለት ነው፡፡

የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ፍ/ቤትም ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ ገደብ የሚያደርጉ ሕጎች በአንድ ንግግር ላይ ያላቸውን ተግባራዊነት በተመለከተ ውሳኔ ሲሰጥ ንግግሩ የተደረገበትን አውድ ለመረዳት የሚያስችሉ፣ ለምሳሌ፣ የክስ መነሻ የሆነው ንግግር የሚገኝበትን ሙሉ ንግግር (the wider discourse in which a statement is made) የመሰሉ መለያ መስፈርቶችን (contextual factors) ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡[55] ለምሳሌ አንድ የንግግር መርሀግብር ወይም ጽሑፍ ሙሉ በሙሉ ወይም ይበልጡኑ (በተደጋጋሚ) በሚባል ደረጃ የጥላቻ ንግግር ይዘቱ፣ የአጠቃላይ መርሀግብሩ ወይም የጽሑፉ ዋና ዓላማ እና መገለጫ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በአጋጣሚ ወይም እግረ-መንገድ የተነሳ፣ ድግግሞሽ የሌለው የመርሀግብሩ ወይም ጽሑፉ ዋና መገለጫ ተደርጎ የማይወሰድ ንግግርም ይኖራል፡፡ ይህን ለመረዳት የክስ መነሻ የሆነውን ንግግር ብቻ በተናጥል በመውሰድ ሳይሆን ጥያቄ የተነሳበት ንግግር የተነገረበትን፣ የተጻፈበትን ሙሉ ንግግር ወይም ጽሑፍ ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡

ከፍ ሲል ከተገለፀው በተጨማሪ፣ እንደ ጥላቻ ንግግር የማይወሰዱ "የትምህርታዊ ወይም ሣይንሳዊ ምርምር አካል" የሆኑ ንግግሮችን በተመለከተ ሊነሳ የሚችል ሌላ ጥያቄ

---

[53] እዚህ ጋር ዐቃቤ ሕግ ክስ በሚመሰረትበት ጊዜ የወንጀል ድርጊት ተደርገው የተቀመጡት ተግባራት ከመፈፀማቸው በተጨማሪ የድርጊቱን ፈፃሚ/ዎች የሐሳብ ክፍል (intention) ሆን ተብሎ ጥላቻን፣ መድሎን ወይም ጥቃትን ማነሳሳት መሆኑን ጭምር ለማስረዳት መዘጋጀት አለበት፡፡ የሓሳብ ክፍልን ማስረዳት ከባድ ቢሆንም ድርጊቶቹ መፈፀማቸው ብቻውን ወንጀል ስለማይሆን እና ይህን የተመለከተም የሕግ ግምት እንዲወሰድ በሕጉ ስላልተገለፅ የድርጊቶቹን መፈፀም እና የሓሳብ ክፍልን የማስረዳት ሽክም በዐቃቤ ሕግ ላይ ይወድቃል ማለት ነው፡፡

[54] የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ አጭር ማብራሪያ፣ ገፅ 3

[55] Therese E. & Simon L., *Free speech or hate speech? A legal analysis of the discourse about Roma on Twitter*, Information & Communications Technology Law, p.2 available at https://www.tandfonline.com/doi/full/10.1080/13600834.2018.1494415

አለ፡፡ ይኸውም የንግግሩ ትምህርታዊነት ወይም ሣይንሳዊነት የሚለየው በምን ዓይነት መስፈርቶች ነው? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት፣ ንግግሩ የባለሙያ አስተያየት እንዲሰጥበት በማድረግ ንግግሩ ምን ያህል ትምህርታዊ/ሣይንሳዊ እንደሆነና በሙያው ተቀባይነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡[56]

### 7.3 ኃይማኖታዊ አስተምህሮ መስለው የሚቀርቡ የጥላቻ ንግግሮች

የኃይማኖታዊ አስተምህሮት አካል የሆኑ ንግግሮችን እንደ ልዩ ሁኔታ ያስቀመጠውን ድንጋጌ[57] በተመለከተ በርካታ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ይኸውም የአዋጁን ክልከላ በመተላለፍ የጥላቻ ንግግር የማሰራጨት ወንጀል ክስ የቀረበበት ተከሳሽ የአዋጁን አንቀጽ 6(1)(መ) መሠረት በማድረግ እንደ ሁኔታው የክስ መቃወሚያ ወይም መከላከያ ቢያቀርብ፣ ንግግሩ የኃይማኖት አስተምህሮ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የሚደረግ የክርክር ሂደት ለፍርድ ቤት ፈታኝ ጭብጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ የሚሆነውም፣ አንደኛ አዋጁ የኃይማኖት አስተምህሮዎችን በልዩ ሁኔታነት ሲያስቀምጥ፣ "ኃይማኖት" ለሚለው ቃል በአዋጁ ውስጥ የተሰጠው ትርጓሜ የለም፡፡[58] ስለሆነም የኃይማኖት አስተምህሮን መሠረት ያደረገ የክስ ተቃውሞ ወይም መከላከያ በሚቀርብ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ሁሉንም መቀበል ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተቋማዊ የሆኑ ኃይማኖቶችን ጨምሮ ሌሎች በግለሰብ ደረጃ ያሉ የኃይማኖት ዓይነቶችን ሁሉ ስለሚያጠቃልል በአዋጁ እንደ ልዩ ሁኔታ የተቀመጠውን ድንጋጌ ወደ መርህነት በመቀየር ሁሉም ዓይነት መከላከያዎች በዚህ መልክ እንዲቀርቡ በር በመክፈት የአዋጁን አፈፃፀም ሊገድብ ይችላል፡፡

እዚህ ነጥብ ላይ በአዋጁ የመጀመሪያ ረቂቅ "*በቅን ልቦና የሚደረጉ ኃይማኖታዊ አስተምሮት ወይም አተረጓጎም* ከሆነ"[59] (አጽንኦት የተጨመረ) በማለት የተቀመጠውን መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡ በቅን ልቦና የተደረጉ እና ያልተደረጉ አስተምህሮዎችን ለመለየት የሚያጋጥመው ችግር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህ ሐረግ ሁሉንም የኃይማኖት አስተምህሮዎች እንደ ልዩ ሁኔታ ለመቀበል ታስቦ እንዳልነበር ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡

የኃይማኖት አስተምህሮን መሠረት ያደረገ መከላከያ በሚቀርብበት ጊዜ ሊነሳ የሚችለው ሌላ ጥያቄ፣ ንግግሩ የኃይማኖት አስተምህሮ መሆን/አለመሆኑን ለማረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ማስረጃ መስማት ውስጥ የሚገባ ስለመሆን አለመሆኑ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ወደ ማስረጃ መስማት ውስጥ የሚገባ ከሆነ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚያስተላልፍ ውጤት ስለሚኖረው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት ስለመንግሥት እና ኃይማኖት መለያየት ከደነገገው ጋር የሚጋጭ ይሆናል፡፡[60]

---

[56] ሆኖም ግን አንድ ንግግር ትምህርታዊ ወይም ሣይንሳዊ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ንግግር አድራጊው ሰው በጉዳዩ ላይ ባለሙያ (ወይም ሥልጠና ያገኘ) መሆን የሚገባው ስለመሆን/አለመሆኑ የተመለከተ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡

[57] አዋጅ ቁ. 1185/2012፣ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 39፣ አንቀጽ 6(1)(መ)

[58] እርግጥ ነው "ኃይማኖት" ለሚለው ቃል ትርጓሜ መስጠት የሚቻል መሆን አለመሆኑ የሚነሳው ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ትርጓሜ መስጠት ይቻላል ቢባል እንኳን፣ ትርጓሜው የተወሰኑ ኃይማኖቶችን በማካተት ሌሎችን የማግለል ውጤት ሊኖረው ስለሚችል በትርጓሜው ላይ ሊቀርብ የሚችል ተቃውሞ ስለመኖሩ ማሰብ ይቻላል፡፡

[59] በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ለመከላከል የወጣ አዋጅ (የመጀመሪያ ረቂቅ)፣ አንቀፅ 6(1)(ሐ)

[60] እዚህ ጋር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጣቸው ውሳኔዎች ሃይማኖታዊ ጉዳዩችን መመልከትን የሚጠይቁ ጉዳዮችን ፍ/ቤቶች ማየት እንደሌለባቸው የወሰነባቸውን የፍርድ ውሳኔዎች ማንሳት

የኃይማኖት አባቶች በጉዳዩ ላይ ምስክርነት እንዲሰጡበት ማድረግን እንደ አማራጭ ማስቀመጥም ብዙ ርቀት የሚወስድ አይመስልም፡፡ ምክንያቱም ለክስ መነሻ የሆነው ንግግር ኃይማኖታዊ አስተምህሮ ስለመሆን አለመሆኑ የተለያዩ አተረጓጎሞች ሊቀርቡ ከቻሉ፣ አንዱን ውድቅ አድርጎ ሌላኛው ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ ይከሰታል፡፡ ይህ ደግሞ፣ የመንግሥት እና ኃይማኖት መለያየት መገለጫ ባህሪያት አንዱ የሆነውንና በመንግሥት በኩል ኃይማኖታዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ኦፊሴላዊ ወይም ይፋዊ እውቅና መስጠትም ሆነ መንፈግ እንዳይኖር የሚከለክለውን መርህ የሚጥስ ይሆናል፡፡[61]

### 7.4 የወንጀል ተጠያቂነት ወጥነት፣ አዝናኝ ቀልዶችና የአተረጓጎም ጥንቃቄ

አዋጁ በአንቀጽ 7(2) እንደተደነገገው፣ "በጥላቻ ንግግሩ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጉዳት የተፈጸመ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ቀላል እስራት ይሆናል፡፡" ይህም ማለት በጥላቻ ንግግር ተነሳስቶ ጥቃቱን የፈፀመ ግለሰብ ጥቃቱን በተመለከተ በመደበኛው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ መሠረት በሚቀርብበት ክስ የሚቀጣ ሲሆን፣ በአንፃሩ ደግሞ የኃይማኖታዊ አስተምህሮዎችን መሠረት በማድረግ የጥቃት መንስዔ የሆነውን ንግግር የተናገረውን ሰው ከተጠያቂነት ነፃ የምናደርግበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል፡፡ ተናጋሪው ነፃ ሆኖ፣ በንግግሩ ተነሳስቶ ጥቃቱን የፈፀመውን ግለሰብ ግን በወንጀል ኃላፊ መደረጉ በሚዛናዊ ዓይን ሲታይ ኢ-ፍትሐዊ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

እንደ ሥነ ጥበብ ወይም ኪነ ጥበብ ውጤት የሚወሰዱ ሥራዎችን በተመለከተም የሚነሳው ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አሁን አሁን እየተለመደ (እየተዘወተረ) የመጣ በተለምዶ አጠራር "*ፕራንክ ማድረግ*" የሚባሉ ሰው የማዝናናት ዓላማ ያላቸው ሥራዎች ይሠራሉ፡፡ በእነዚህ ሥራዎች ውስጥ ጥላቻን የሚያንጸባርቅ አገላለጽ የሚገኝ ከሆነና አንድን ግለሰብ ወይም ቡድን ዝቅ የማድረግ ወይም የሚያስጠላ ዓላማ ያለው አገላለጽ ከሆነ የጥላቻ ንግግር ውስጥ የሚካተት ስለመሆኑ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡

## 8. ከአዋጁ አፈጻጸም አንፃር የተቋማትና አገልግሎት ሰጭዎች ኃላፊነት

የአዋጁ አንቀጽ 8 ተቋማትና አገልግሎት ሰጭዎች የሚኖራቸውን ኃላፊነት ደንግጓል፡፡ ማንኛውም የማኅበራዊ ሚዲያ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት በአንቀጽ 4 እና 5 ሥር የተከለከሉ ንግግሮች እንዳይተላለፉ ወይም እንዳይሰራጩ የመቆጣጠርና የመግታት፣ የተከለከሉ ንግግሮችን በተመለከተ ጥቆማ ሲደርሰው እና ጥቆማው አሳማኝ ሲሆን ንግግሩን በአፋጣኝ የማስወገድ ወይም ከስርጭት የማውጣት ግዴታ አለበት፡፡ በተጨማሪም፣ ማንኛውም የማኅበራዊ ሚዲያ አገልግሎት ግዴታውን ለመወጣት

ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ የስራ ክርክሮችን አስመለክቶ የሰበር ችሎቱ በቅፅ 8 ሰበር መዝገብ ቁጥር 18419 የሰጠውን ውሳኔ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል

[61] Secularism, among other things, prohibits a state from indulging in the promotion of religious views. (*See* Charles Taylor, *The Meaning of Secularism*, at 23,available at: http://iasc-culture.org/THR/archives/Fall2010/Taylor_lo.pdf ; *see* also, Abdelwahab El- Affendi, *Beyond Secularism*: *Sectarian Conflict and the Resilience Challenge for the African State*, at.8, available at: https://www.africaportal.org/dspace/articles/beyond-secularism-sectarian-conflict-and-resilience-challenge-african-state

የሚያስችለው አሠራርና ፖሊሲ ሊኖረው እንደሚገባ፤ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ባለሥልጣን የማኅበራዊ ሚዲያ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች በአዋጁ የተደነገገውን ግዴታቸውን ባግባቡ እንዲወጡ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ግዴታ እንዳለበትና የሐሰት መረጃ ስርጭትና ጉዳትን ለመከላከል የሚረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሀግብሮችን በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲያደርግ፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል የሚረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሀ ግብሮችን በማዘጋጀት ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የተቋማትና የአገልግሎት ሰጪዎችን ኃላፊነት ዝርዝር የሚደነግግ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊወጣ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በአዋጁ የተደነገገውን ግዴታ አለመወጣት ሊያስከትል የሚችለው የፍትሐብሔር ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን የማኅበራዊ ሚዲያ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች በአዋጁ የተቀመጠውን ግዴታቸውን ባግባቡ መወጣታቸውን እየተከታተለ በዓመት ሁለት ጊዜ ለሕዝብ ይፋ የሚሆን ሪፖርት እንደሚያዘጋጅ ተገልጧል፡፡[62] ይህም የማኅበራዊ ሚዲያ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ላይ የተጣለው ግዴታ በቅጣትና በወንጀል ተጠያቂነት ላይ ያተኮረ ሳይሆን፣ እነዚህ ተቋማት ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ እንዲንቀሳቀሱ የሞራል ተጽዕኖ ለማሳረፍና ከዚያም አልፎ ለሚኖርባቸው የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የታሰበ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

የማኅበራዊ ድረገጾችን ሚና በሚመለከት፣ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በማኅበራዊ የትስስር ገጾች የሚተላለፉ የጥላቻ መልዕክቶች ብዙ ዋጋ ሲያስከፍሉ ታይተዋል፡፡ ምንም እንኳን የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮች ሰብዓዊ መብቶችን በሚመለከት በቀጥታ ኃላፊነት ባይኖርባቸውም፤ ምንም ዓይነት ተጠያቂነት የለባቸውም ማለት አይደለም፡፡ በአንፃሩ ሰብዓዊ መብቶችን በሚመለከት የጎንዮሽ የሰብዓዊ መብት ግዴታ (horizontal obligation of human rights) ስላለባቸው፣ ይህንንም በሚመለከት፣ የመጠበቅ (duty to protect) እና የመከታተል ኃላፊነቱን መንግሥት መወጣት ይኖርበታል፡፡[63] በአሁኑ ወቅት ማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮች በበይነመረብ በሚገኝ ይዘት ላይ አስተዳዳሪ ('governors of online content') ሆነዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ የሲሊከን ሸለቆ ግዙፍ ኩባንያዎች (Silicon Valley tech companies ) ለሕግ አይገዙም ማለት አይደለም፡፡

በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች ሕግ የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮች የመናገር ነፃነትን እንዲያከብሩ እና የጥላቻ ንግግርን ከፕላትፎርሞቻቸው ወዲያውኑ እንዲያወርዱ በ ተ.መ.ድ. የቢዝነስ እና ሰብዓዊ መብቶች መሪ መርሆዎች (UN Guiding Principles on Business and Human Rights) መሠረት ግዴታ አለባቸው፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል በወጣው አዋጅ መሠረት በተለይም በአንቀጽ 8(2) መሠረት ሕገወጥ የሆነን ይዘት በ 24 ሰዓት ውስጥ ከፕላትፎርሞቻቸው ማውረድ ወይም ማረም እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡[64]

---

[62] የመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 68 (2)ሠ ይመልከቱ፡፡ በተጨማሪም የጥላቻ ንግግርንና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 1185/2012 አንቀጽ 8 (4)ን ይመልከቱ፡፡

[63] ዮሐንስ እንየው አ., (2013), *በኢትዮጵያ የጥላቻ ንግግርን በመከላከል ረገድ የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮች ሚና* Abyssinia Law Blog, p. 10

[64] ዝኒ ከማሁ

የይዘት እርማት (content moderation) ማለት አስቀደሞ በተወሰነ የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮች የማኅበረሰብ መተዳደሪያ ደንቦች (community standards) መሠረት አንድን ይዘት ሕጋዊ ነው አይደለም የሚለውን የምንወስንበት ሂደት ነው፡፡ ይህንን ይዘት የሚመረምሩ አካላት የይዘት አራሚዎች (content moderators) እንደመሆናቸው የይዘት ጥበቃ ('digital gatekeepers') ሚና አላቸው፡፡ የይዘት እርማት አንድን ተጠቃሚ የሚረብሹ ነውረኛ እና ሕገ ወጥ ይዘቶችን ሪፖርት በማድረግ እንዲወገዱ ያስችላል፡፡ ይህንን በማድረጋቸውም ፕላትፎርሞቹ መልካም ስማቸውን ለአዲስ ተጠቃሚዎች፣ ደጋፊዎች እና ለኅብረተሰቡ ያሳያሉ፡፡

የይዘት እርማት ጥያቄ አፈጻጸምና አሠራር እንደየ ፕላትፎርሞቹ ቅርጽ እና ተቋማዊ አደረጃጀት ይለያያል፡፡ በዚህ ረገድ ሮቢ ካፕላን ሦስት ዋና ዋና የይዘት እርማት መንገዶችን አመልታለች፡፡[65] የመጀመሪያው መንገድ በእጅ ሥራ የሚከናወን (*artisanal* approach) ሲሆን የፕላትፎርሞቹን ይዘት የሚመረምሩ ሰዎችን በመሰየም በሰው ጉልበት እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ እንዲህ ዓይነት መንገድ የሚከተሉ የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮችን በሚመለከት፣ ለምሳሌ፡ ሚዲየም (Medium) እና ቬሚዮ (Vimeo) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በእጅ እርማት ማከናወን ለአቅራቢያዊ አውድ ምቹ በመሆን ይወደሳል፡፡[66] ሁለተኛው ዘዴ ማኅበረሰብ-መር የሆነ (*community-reliant* approach) ሲሆን እርማቱን የሚያከናውኑት በአንድ ኩባንያ ውስጥ ያሉ ጥቂት ግለሰቦች ከፈቃደኛ የፕላትፎሙ ተጠቃሚዎች ጋር በመሆን ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ዊኪሚዲያ (Wikimedia) እና ሬዲት (Reddit) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የዚህ ዘዴ መልካም ጎኑ የይዘት እርማት በሚከናወን ጊዜ ተጠቃሚዎችም አብረው መሳተፍ መቻላቸው ነው፡፡[67]

ሦስተኛው መንገድ የኢንዱስትሪ ዘዴ (industrial approach) የሚሰኝ ነው፡፡ እርማቱ የሚከናወነው በጣም ሰፊ በሆነ ተቋማዊ አሠራር እና የሥራ ተዋረድ ባለው ሁኔታ ነው፡፡ ይህ አሠራር ብዙ የይዘት አራሚዎችን ቀጥረው በሚያሠሩ ፕላትፎርሞች ያሉት ሲሆን፣ የራሳቸውን የፖሊሲ ቡድን ለብቻ ያዋቀሩ ትልቅ ኩባንያዎችን ይጨምራል፡፡ ለምሳሌ ፌስቡክ (Facebook) እና ዩቲዩብ (YouTube) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ይህ ዘዴ ስፋት ያለው ከመሆኑ አኳያ ሰው ሠራሽ ልህቀት (artificial intelligence) ዘዴ በመጠቀም የጥላቻ ይዘት ያላቸውን መልዕክቶች እንዲለዩ ለማድረግ ያስችላል፡፡[68]

የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮች የራሳቸው የሆነ የጥላቻ ንግግር መከላከያ ደንብ አላቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ፌስቡክ ያወጣው የማኅበረሰብ መመሪያ (Community Standard) የጥላቻ ንግግርን ሲተረጉም፣ "አንድን ሰው ተለይተው በታወቁ ምክንያቶች ማለትም ዘር፣ ቀለም፣ ጎሳ፣ ዜግነት፣ እምነት፣ ጾታ ወዘተ መሠረት በማድረግ የሚደረግ ጥቃት" እንደሆነ ይናገራል፡፡ ጥቃት ሲባልም "ነውጠኛ የሆነ እንዲሁም ሰብዓዊነትን የሚያጠፋ ንግግር፣ የበታችነትን የሚያጎናጽፋ አገላለጾች፣ መከልከል ወይም የማግለል ጥሪዎችን" ይጨምራል፡፡

የፌስቡክ የጥላቻ ንግግር ትርጓሜ ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት አንፃር 'ማነሳሳት' እና 'ማሰብ' የሚሉ ቅድመ ሁኔታዎችን አላስቀመጠም፡፡ ሆኖም ግን ለይዘት አራሚዎች ይረዳ ዘንድ የጥላቻ ንግግር ይዘቶችን በሦስት ደረጃ ለማስቀመጥ ሞክሯል፡፡ የመጀመሪያው

[65] ዝኒ ከማሁ
[66] ዝኒ ከማሁ
[67] ዝኒ ከማሁ
[68] ዝኒ ከማሁ

ደረጃ (Tier 1) ነውጥን የሚቀሰቅሱ ንግግሮች (contents/speeches with violent content) ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ አንድን ሰው ወይም ቡድን በእንስሳ ወይም በበሽታ መሰየም፡፡ በሁለተኛ እርከን (Tier 2) የሚቀመጡ ንግግሮች ደግሞ የበታችነት ስሜትን ለማጎናጸፍ የሚደረጉ ንግግሮች (contents that promote inferiority) ናቸው፡፡ ለምሳሌ፦ በጾታ ምክንያት አንድን ሰው ደካማ እንደሆነ የሚገልጹ ንግግሮች፡፡ የመጨረሻው ምድብ ደግሞ (Tier 3) አንድን ሰው በሚገኝበት ቡድን ምክንያት እንዲጠቃ የሚያደርጉ (contents that targets individuals on their protected status) ናቸው፡፡ ለምሳሌ፦አንድን ቡድን በዘውገ ማንነቱ ምክንያት እንዲገለል የሚደረጉ ቅስቀሳዎች (calls of segregation) ተጠቃሽ ናቸው፡፡[69]

ምንም እንኳን የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮች በዋናነት በኮርፖሬት ፍላጎት እየተመሩ ገቢንና ትርፍ ማካበትን ቢያስቀድሙም፣ የጥላቻ ንግግር እንዳይንሰራፋ እና ጉዳት እንዳይደርስ በፍጥነት የእርምት እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡ ይህንንም በሚመለከት የቀድሞው የተ.መ.ድ. የመናገር ነፃነት ልዩ መልክተኛ ዴቪድ ኬይ የኢትዮጵያን ጉብኝት ካጠናቀቁ በኋላ በወጣው የማጠቃለያ ሪፖርት ላይ የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮች በኢትዮጵያ መደበኛ የሆነ እና ቀጣይነት ያለው ክትትል እንዲያደርጉ ማሳሰቢያ ቀርቧል፡፡[70]

## 9. የጥላቻ ንግግር ሕግ ጥሰትን በሚመለከት የፍርድ ቤቶች ቅጣት የመወሰን ሚና

የጥላቻ ወንጀል ተጠያቂነትንና የቅጣት ዓይነቶች በአዋጁ አንቀጽ 7 ሥር ተደንግገዋል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 4 የተመለከተውን የጥላቻ ንግግር ወንጀል መፈጸም እስከ ሁለት ዓመት የሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከመቶ ሺህ ብር ያልበለጠ መቀጮ እንደሚያስቀጣ በአንቀጽ 7(1) ተደንግጓል፡፡ ፣ በአንቀጽ 4 የተከለከሉት ተግባራት በመፈጸማቸው የተነሳ በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ ወይም የተሞከረ ከሆነ በአንቀጹ የተከለከሉትን ተግባራት የፈጸመ ሰው እንደነገሩ ሁኔታ እስከ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሚቀጣ አንቀጽ 7(2) ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ የወንጀል ተጠያቂ የሆነ ሰውን ለማረም የተሻለ ነው ብሎ ሲያምንና የተከለከለው ተግባር በመፈጸሙ በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት ያልተፈጸመ ወይም ያልተሞከረ ከሆነ፣ ሁከት ወይም ግጭት ያልተከሰተ እንደሆነ በፍርድ ቤቱ ሥልጣን በእስራት ምትክ የማኅበረሰብ አገልግሎት ሥራን በአማራጭ ቅጣትነት ሊወስን እንደሚችል አንቀጽ 7(2) ይደነግጋል፡፡

ፍ/ቤቶች ቅጣትን በሚወስኑበት ወቅት በተለይም በአዋጁ አንቀጽ 7(6) ላይ ከተቀመጠው በተጨማሪ በመደበኛው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 178 እና ተከታዮቹ፣ አንቀጽ 183 እና ተከታዮቹ፣ አንቀጽ 189 (የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ደንቦች) እንዲሁም አን 190 እና ተከታዮቹ (ቅጣትን በገደብ ስለማቆም) የተደነገጉትንና በተሻሻለው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሠረት የተቀመጡትን መርሆዎች ተፈጻሚ የሚያደርጉ መሆኑም ይታወቃል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ በአንቀጹ የተቀመጡትን ቅጣቶች በዚህ መጠን ማስቀመጥ ያስፈለገው በተጠቀሱት ወንጀሎች የሚሳተፉ አካላትን

[69] ዝኒ ከማሁ

[70] ዝኒ ከማሁ

ለማስተማር በቂ እና ተመጣጣኝ ናቸው በሚል እሳቤ ነው፡፡ ቅጣት በማግዘፍ ብቻ ወንጀሉን ለማስወገድ ከመሞከር ይልቅ የግንዛቤ ማጎልበቻና የእርምት ዕድል በመስጠት ወንጀሉ የሚቀንስበትን ብሎም የሚወገድበትን አግባብ በሂደት መቀየስ አግባብነት አለው፡፡ ለዚህም ነው ፍርድ ቤቶች ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ቅጣቱ ላይ ሳይሆን ማረሙ ላይ ማተኮር እንዳለባቸው በሰፊው የሚታመነው፡፡

የሰዎች አጠቃላይ ሰብዓዊ መብቶች የሚከበሩትና በሕግ ጥበቃ የሚደረግላቸው፣ ሰብዓዊ ክብርና ስብእና ተከብሮ በሰዎች መካከል መስተጋብር በመፍጠር በሰላም እንዲኖሩ ለማድረግ ነው፡፡ ሰብዓዊ መብቶች ባልተከበሩበት ሁኔታ ወይም ሰብዓዊ መብቶች ዓላማቸውን በሳተ መልኩ ተለጥጠው ተግባራዊ እንዲሆኑ በሚሞከርበት ጊዜ ሰዎች በሰላም እየኖሩ ደህንነታቸው ሊጠበቅ አይችልም፡፡ መብቶች እና ነፃነቶችን በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል በመብቶቹ እና ነፃነቶቹ ላይ ሊደረጉ የሚገባቸው ገደቦችም አብረው መታየት አለባቸው፡፡ የሰዎችን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ የሚደነገጉ ሕጋዊ ገደቦች ውስጥ የጥላቻ ንግግር ክልከላና ተጠያቂነት ሥርዓትም ከነዚህ ገደቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ በእርግጥ እስከ አሁን ድረስ በፍርድ ቤት የተያዙ ጉዳዮች ባይኖሩም፣ ሕጉ አዲስ በመሆኑ ግንዛቤን ማዳበርና ተከታታይ ሥልጠና ማካሄድ አግባብነት ካለው አካል ይጠበቃል፡፡

## 10. አንኳር ነጥቦችና መደምደሚያ

ቀደም ሲል እንደገለፀው፣ የሰው ልጅ በተፈጥሮው የሚያስብ እና ያሰበውንም በተለያዩ መንገዶች የሚገልፅ እና የሚያስተላልፍ ፍጡር ነው፡፡ ስለሆነም ይህንን በተፈጥሮ ያገኘውን ስጦታና ችሎታ ያለምንም እንቅፋት ይጠቀም ዘንድ፤ ሓሳብን በነፃነት ለመግለጽ መብት በተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ከለላና ጥበቃ ተደርጓል፡፡ ሆኖም ግን (ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትን ጨምሮ) የሰብዓዊ መብቶች በባህሪያቸው ፍፁማን ስላይደሉና የመብቶቹ አጠቃቀም የሌሎችን መብት ወይም ጥቅም መንካት ስለሌለበት እንደሌሎቹ መብቶች ሁሉ ይህም ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ገደብ እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በዓለምአቀፍም ሆነ በአገራችን በተለያየ መልኩ የሰዎችን ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትንም ሆነ የሰዎችን መልካም ስም፣ የሕዝቦችን ሰላም፣ ፀጥታና ደህንነትን የሚጠብቁ ሕግጋት በተለያዩ ጊዜያት ወጥተው ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን መከላከልና መቆጣጠርን ታሳቢ ያደረገው ሕግ አንዱ ነው፡፡

ነገር ግን ሓሳብን በነፃነት ለመግለጽ መብት ጥበቃ በሚያደርጉ ሕጎች እና በዚህ መብት ላይ ገደብ በሚያስቀምጠው (የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚወጣ) ሕግ መካከል ያለውን መስተጋብር በተመለከተ ተቃራኒ ሓሳቦች አሉ፡፡ ከላይ እንደተመለከተው፣ በአንድ በኩል፣ የጥላቻ ንግግሮች በአገራት ሰላም እና መረጋጋት እንዲሁም በሰው ልጆች ደህንነት ላይ በሚያስከትሉት ከፍተኛ አደጋ ምክንያት፣ ይህንን ድርጊት ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ ገደቦች ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የሚገልፁ ወገኖች አሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ስለጥላቻ ንግግር ምንነትን የሕግ ትርጓሜ ለመስጠት በሚደረግ ጥረት ውስጥ በሕግ ጥበቃ እና እውቅና ባገኘው ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ አላስፈላጊ ጫና የሚፈጥር መሆኑን በማስረዳት፣ ሓሳብን በመግለጽ ነፃነት ላይ ገደብ የሚያደርጉ ሕጎችን መውጣት የሚቃወሙ ወገኖች አሉ፡፡ ይህ ጥያቄ የኢትዮጵያን ሕግ በተመለከተም የሚነሳ በመሆኑ፣ ሓሳብን በነፃነት ለመግለጽ መብት ጥበቃ በሚያደርጉ ሕጎች እና በዚህ መብት ላይ ገደብ በሚያስቀምጠው የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው ሕግ መካከል ያለውን መስተጋብርና ሚዛን መመርመር ተገቢ ነው፡፡

በዓለምአቀፍ ደረጃ ሓሳብን በነፃነት ለመግለጽ መብት ዕውቅና በመስጠት ሕጋዊ ጥበቃ ያደረገው ሰነድ ሁሉአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (1948 እ.ኤ.አ) /Universal Declaration of Human rights (UDHR) ነው፡፡ ከዚያ በመቀጠል በ1966 ዓ.ም የወጣው ዓለምአቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች የቃል ኪዳን ስምምነት ሲሆን የዚህ ስምምነት አንቀጽ 19 ለዚህ መብት እውቅና ከመስጠት ባሻገር በአንቀጽ 20 ማንኛውም የጦርነት ፕሮፓጋንዳም ሆነ ጥቃትን የሚያነሳሳ ማንኛውም የዘር፣ የብሔር ወይም ኃይማኖታዊ ጥላቻን መሰበክ በሕግ የተከለከለ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይህ ስምምነት ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትን በተመለከተ፣ ከላይ ከተጠቀሰው (እ.ኤ.አ) ከ1948 ሁሉ አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ በይዘት ረገድ ልዩነት አለው፡፡ ምክንያቱም መግለጫው መብቱን ብቻ ሲያስቀምጥ ስምምነቱ ግን መብቱን ከማክበርና እውቅና ከመስጠት በተጨማሪ መብቱ ሊገደብባቸው የሚችሉትንም ልዩ ሁኔታዎች አካቷል፡፡

ከላይ በክፍል 4 ላይ እንደተገለፀው፣ ሓሰብን በነፃነት በመግለጽ መብት ላይ የሚጣል ገደብ ሊያሟላ የሚገባውን መስፈርት በሚመለከት፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች የቃል ኪዳን ስምምነትን አፈጻጸም ለመከታተል የተቋቋመው የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ አጠቃላይ ትርጉም ቁ. 34 (General Comment # 34) የገለፃቸው ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል፡፡ በእነዚህ አራት መርሆች (ማለትም፣ የሕጋዊነት መርህ፣ ምክንያታዊ ተቀባይነት መርህ፣ ዴሞክራሲያዊ አስፈላጊነት እና የተመጣጣኝነት መርህ) መሠረት ሓሰብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ ገደብ በማስቀመጥ ማሳካት የተፈለገው ዓላማና ግብ፣ እና በሚጣለው የገደብ መጠን መካከል ተገቢውን ሚዛን መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

በ1987 ዓ.ም ፀድቆ ሥራ ላይ የዋለው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 29 ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የአመለካከትና ሓሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት እንዳለው በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን መልካም ስም ለመጠበቅ፣ የጦርነት ቅስቀሳዎችን ለመከላከል እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሲባል ገደብ እንደሚደረግበት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 29(6) ተደንግጓል፡፡

ከላይ በክፍል 6.2 እንደተገለፀው የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃዎችን ማሰራጨት ሕግ (አዋጅ ቁ. 1185/2012) ይህንኑ ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ገደብ እንዲኖረው ያደረገ አዲስ የሕግ ማዕቀፍ ነው፡፡ የጥላቻ ንግግር ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ውስጥ ሊካተት የሚችል መሆን/አለመሆኑን አስመልክቶ የሚነሳውን ክርክር ስንመለከት፣ የጥላቻ ንግግር በይፋ የአንድን ግለሰብ ወይም ቡድን ብሔር፣ ኃይማኖት፣ጾታ፣ ወዘተ መሠረት ያደረገ ጥላቻን የሚያንጸባርቅ ወይም ጥቃትን የሚያበረታታ ንግግር ማለት ተደርጎ የሚወሰድ ከሆነ ይህን መሰሉ ንግግር ሓሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው፡፡

በተለይም አንቀጽ 29 ሥር ከተቀመጡት ንዑሳን ድንጋጌዎች/ቁጥሮች ማለትም ከንዑስ ቁ. 1-6 ድረስ ያሉት ማንኛውም ሰው ሓሳቡን በነፃነት የመግለጽ መብት እንዳለውና ይህንንም መብቱን ያለማንም ጣልቃ ገብነት መጠቀም እንደሚችል ነገር ግን በሕግ ገደቦች ሊጣሉ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን፣ የአንቀጹ ንዑስ ቁጥር 7 ሕጉ ተጥሶ ከተገኘ ማንኛውም ሰው ተጠያቂ እንደሚሆን መደንገግ ሲገባው፣ "ማንኛውም ዜጋ" የሚሉ ቃላትን የተጠቀመ በመሆኑ ጥንቃቄ የተመላበት አተረጓጎምን መከተል ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም፣ ከላይ በተራ ቁጥር 6.5 እንደተገለፀው ይህን የሕገ መንግሥት ድንጋጌ አንድም ይፋዊ ባልሆነ የሕግ መንግሥት አንቀጽ ማሻሻያ ማለትም በሕገ መንግሥት ትርጉም፣ ወይም በይፋዊ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሥርዓት መሠረት

የድንጋጌው የተሳሳተ ደረቅ ንባብ (literal reading) ለሚያስከትለው ችግር መፍትሔ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

የጥላቻ ንግግርንና ሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ውስጥ የተካተቱ አንዳንድ ሐሳቦችና ቃላት የግልፅነት ችግር አለባቸው፡፡ ከነዚህም መካከል እንደ ጥላቻ ንግግር ስለማይቆጠሩ ንግግሮች የተደነገጉትን ልዩ ሁኔታዎች (exceptions) እናገኛለን፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 6 የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃ ማሰራጨት የተከለከለ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በልዩ ሁኔታ የሚታዩ ነጥቦችን የሚዘረዝር ሲሆን አንድ ንግግር እንደ ጥላቻ ንግግር እንዳይወሰድ ከሚያደርጉ ምክንያቶች ውስጥ አንደኛው ንግግሩ በንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የትምህርታዊ ወይም ሣይንሳዊ ምርምር አካል እንደሆነ ነው፡፡"

በአዋጁ እንደ ጥላቻ ንግግር ተደርጎ በልዩ ሁኔታነት የተቀመጠው ሌላ ልዩ ሁኔታ ንግግሩ "የዜና ዘገባ፣ ትንታኔ ወይም ፖለቲካ ትችት አካል እንደሆነ ነው፡፡" በተጨማሪም አንድ ንግግር የኪነጥበብ፣ ትወና ወይም መሰል የሥነጥበብ ውጤት ከሆነ እንደ ጥላቻ ንግግር አይወሰድም፡፡ እነኝህ ዓይነት የሥነጥበብ ሥራዎች እንደ ጥላቻ ንግግር የማይወሰዱት፣ ሥራዎቹ ጥላቻን፣ መድሎን ወይም ጥቃትን ከማነሳሳት ይልቅ ሰውን ማዝናናት ላይ ያተኮሩ ናቸው በሚል እሳቤ ነው፡፡

ሌላኛው በአዋጁ ውስጥ በተካተቱት ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ እንደ ጥላቻ ንግግር እንደማይወሰድ የተገለፀው የኃይማኖታዊ አስተምህሮት አካል የሆነ ንግግር ነው፡፡ ይህም አዋጁ የሚያስቀምጣቸውን ክልከላዎች ከአስፈላጊነታቸው እና ተመጣጣኝነታቸው ጋር ሚዛናዊ የማድረግ አጠቃላይ መርህ አንድ አካል ነው፡፡ ቀደም ሲል በተራ ቁጥር 7.3 እንደተገለፀው፣ ይህ ልዩ ሁኔታ የአዋጁ ክልከላ እና አተገባበር በዜጎች የኃይማኖትና እምነት ነፃነት ላይ ሊኖረው የሚችለውን አሉታዊ ውጤት ለማስወገድ የተደነገገ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስለሆነም፣ ከላይ በተራ ቁጥር 7 እንደተገለፀው፣ ልዩ ሁኔታዎችን በሚመለከት ሊያጋጥሙ ለሚችሉ የትርጉምና የሕግ አተገባበር ችግሮችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች ተገቢው ትኩረት እንዲሰጥ ይጠበቃል፡፡

የአዋጁን የልዩ ሁኔታ ድንጋጌዎችም ሆነ ሌሎች የአዋጁን አንቀጾች በመተግበር ሂደት የቃላት/ሐረጎች ግልፅነት ችግር በሚያጋጥምበት ጊዜ፣ ፍርድ ቤቶች የአዋጁን ዓላማ ሊያሳካ በሚችል መንገድ ትርጉም እንደሚሰጡ ይጠበቃል፡፡ ማለትም በአንድ በኩል በዜጎች መብቶች ላይ አላስፈላጊ ጫና (መጣበብ) በማያስከትል ሁኔታ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የጥላቻ ንግግርን በመከላከል እና በመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ላይ እንቅፋት በማይፈጥር ሁኔታ እየተረጎሙ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይም በልዩ ሁኔታ ድንጋጌዎች አተገባበር ወቅት፣ ከተጠያቂነት ነፃ ስለመሆን/አለመሆናቸው አሻሚ የሆኑ ንግግሮች በሚያጋጥሙበት ጊዜ፣ የትኩረት አቅጣጫው ድርጊቶቹ ላይ ብቻ ሊገደብ አይገባም፡፡ ይልቁንም፣ የንግግር አድራጊውን ዓላማ ለመረዳት የሚያስችሉ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባትና የአዋጁን ዓላማ ሊያሳካ በሚችል መንገድ ሕጉ መተግበር ይኖርበታል፡፡ ■